# ርኅሩኅ ሁን

## ሉቃስ 1-13

### አዳኙን ወደ መምሰል በበለጠ እንድናድግ
### የቀረበ ጥሪ

ጽሑፍ፡- ዋረን ድብልዩ ዌርዝቢ

ትርጉም፡- በግርማዊ

አርማት፡- በዓለማየሁ ማሞ

Copyright © 1996 by SIM Addis Ababa, Ethiopia. Originally published in English under the title of BE COMPASSIONATE. Copyright © 1988 by SP Publications, Inc., Wheaton, Illinois USA. All rights resrved.

# ማውጫ

መግቢያ

1. መልካሙን የምሥራች ስማ!......1
(ሉቃስ 1)
2. ጌታ መጣ!......14
(ሉቃስ 2)
3. እነሆ የእግዚአብሔር ልጅ!......27
(ሉቃስ 3–4)
4. ኢየሱስ በሰው ሕይወት ላይ የሚያመጣው ለውጥ ......40
(ሉቃስ 5)
5. አዲስ የሆነ ምን አለ? ሁሉም! ......51
(ሉቃስ 6)
6. ተግባራዊ ርኅራኄ ......64
(ሉቃስ 7)
7. ስለ እምነት የተሰጡ ትምህርቶች ......75
(ሉቃስ 8)
8. ሁለገብ አገልግሎት......87
(ሉቃስ 9)
9. ክርስቲያን ምን ማድረግ ይገባዋል?......100
(ሉቃስ 10)
10. የሕይወትን ትምህርቶች መማር......111
(ሉቃስ 11)
11. አማኝ ሆይ፥ ተጠንቀቅ!......124
(ሉቃስ 12)
12. ጥያቄዎችና መልሶች......137
(ሉቃስ 13)

# መግቢያ

በጠለቀ የፍልስፍና እውቀታቸው የሚደነቁት ፍሬድሪክ ኒቼ፥ «ርኅራኄ ወደ ቁልቁል የሚገፋ ባሕርይ ነው፤ ምክንያቱም አንድ ሰው በሚራራበት ጊዜ ኃይሉን ያጣል» ሲሉ ገልጸዋል።

ኒቼ አዶልፍ ሒትለር በተወለደበት ዓመት ሲያብዱ፥ ሒትለር ግን የእርሳቸውን ፍልስፍና አራመደ። ሌሎችን ሰዎች ንቆ ለብቻው መቆምን መረጠ። በተለይም ደካሞችንና የአካል-ጉዳተኞችን በመናቅ፥ እነርሱን የሚያጠፋበትን መርሐ-ግብር ነደፈ።

ሮበርት ፔን፥ «በበዓል ጊዜያት እንኳ ብቻውን ይሆን ነበር! ከእርሱ ጋር ሲገናኙ የስሜት ተለምዶአዊ አካሄድ ክፉኛ ያሽቆለቁላል... ይህ ሰው ከሌሎች ሰዎች ለመራቅ ቆርጦ ነበር» በማለት የአዶልፍ ሒትለርን ሕይወትና ሞት በሚቃኘው መጽሐፋቸው በገጽ 416 አስፍረዋል።

ይህ ከርኅሩኁ ኢየሱስ ክርስቶስ ምንኛ የሚቃረን ነገር ነው! ሐኪሙ ሉቃስ በጻፈው ወንጌል ውስጥ ጌታችን ቀራጮችንና ኃጢአተኞችን ጨምሮ ከሰዎች ጋር እንደተባበረ አድርጐ ይገልጸዋል፤ በዚህም የተጐዱትን ወገኖችና የደካሞችን ሸክም ተጋርቷል። ኢየሱስ ርኅራኄ የጥንካሬ እንጂ የደካማነት ምልክት እንዳልሆነና የእግዚአብሔርን ኃይል በሚያፈቅር ልብ ውስጥ እንደሚፈስ በማያሻማ መልኩ አረጋግጦአል። ሌሎች ፕላኔቶች ሰው የሰፈረባቸው ከሆኑ የምንኖርበት ዓለም ከነዋሪዎቻቸው መካከል የአእምሮ ሕመም የተጠናወታቸውን ግለሰቦች ለማከማቸት እየተጠቀሙ ሳይሆን እንዳልቀረ የተናገረው እውቁ ደራሲ ጆርጅ በርናርድ ሾው ይመስለኛል። ዓለማችን የፍቅር፥ የዳሰሳና የማጽናኛ ቃል በሚያስፈልጉአቸው ሰዎች የተሞላች ነች። ኢየሱስ ሕዝቡን በዚህ ምድር ያስቀመጠበት ምክንያት ዓለሙ እርሱ እንደሚጠነቀቅለት እንዲያውቅ ነው።

የሰጠንም ትእዛዝ፥ «ርኅሩኆች ሁኑ!» የሚል ነው።

ዋረን ደብልዩ ዌርዝቢ

# የሉቃስ ወንጌል አስተዋጽኦ

ቁልፍ አሳብ፡- ጌታችን እንደ ሰው ልጆች የተጓዘባቸው መንገዶች

ቁልፍ ጥቅስ፡- 19፡10

መግቢያ፡- 1፡1-4

## ዋና ዋናውን አሳብ መግለጫ በአጭሩ

I. ከሰማይ ወደ ምድር የተደረገ ጉዞ - 1፡5-4፡13

ሀ. የልደት ማስታወቂያዎች (1፡5-56)

ለ. የሕፃናቱ መወለድ (1፡57-2፡20)

ሐ. የኢየሱስ የልጅነትና የወጣትነት ጊዜያት (2፡21-52)

መ. የኢየሱስ ጥምቀትና ፈተናዎች (3፡1-4፡13)

II. በገሊላ አውራጃ ሁሉ የተመላለሰበት ጉዞ -4፡14-9፡17

III. ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገው ጉዞ - 9፡18-19፡27

IV. በኢየሩሳሌም ያከናወነው አገልግሎት- 19፡28-24፡53

# መልካሙን የምሥራች ስማ!

## ሉቃስ 1

ለሰው ሁሉ መልካሙን የምሥራች በሚያበስሩ አሳቦች የተሞላ መጽሐፍ የጻፈ ሰው ቢኖር እርሱ ሐኪሙ ሉቃስ ነው። ቁልፍ መልእክቱም፥ «የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና» የሚል ነው (19፡10)። ሉቃስ ኢየሱስ ክርስቶስን በኃጢአተኞች መካከል ሊኖር፥ ሊወዳቸው፥ ሊረዳቸውና ሊሞትላቸው እንደ መጣ ርኅሩኅ የሰው ልጅ አድርጎ ያቀርበዋል።

በዚህ ወንጌል ውስጥ ግለሰቦችና ጭፍሮች፥ ሴቶችና ሕፃናት እንዲሁም ወንዶች፥ ድሆችና ሀብታሞች ብሎም ኃጢአተኞችና ቅዱሳን ይገኛሉ። ሉቃስ አጽንኦት የሰጠው የኢየሱስ ክርስቶስና የማዳኑ ሥራ አጽናፍን የሚያጠቃልል በመሆኑ፥ ይህ መጽሐፍ ለሁሉም ሰው መልእክት አለው፤ «ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች» (2፡10)።

ሐኪሙ ሉቃስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቻ ተጠቅሶአል፤ ይኸውም በቈላስይስ 4፡14፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡11 እና ፊሊሞና ቁጥር 24 ነው። ሉቃስ የሐዋርያትን ሥራ መጽሐፍ ከመጻፉም በላይ (ሉቃስ 1፡1–4ን ከሐዋርያት ሥራ 1፡1 ጋር አስተያይ)፥ ከሐዋርያው ጳውሎስም ጋር ተጉዞአል (በሐዋርያት ሥራ 16፡10–17፤20፡4–15፤21፡1–18 እና 27፡1–28፡16 ብዙ ቁጥር የሚያመለክቱትን ቃላት ተመልከት)። ምናልባትም አሕዛብ (ቈላስይስ 4፡11ን እና 14ን አስተያይ) ሆኖ የሕክምና ትምህርት የተከታተለ ሳይሆን አይቀርም። መጽሐፉን በሁለት በጣም የታወቁ ሕፃናት የልደት ዝርዝር ዘገባዎች መጀመሩ የሚያስደንቅ አይሆንም። ኢየሱስ ለምስኪኖች ለመራራት በወሰደው ከፍተኛ አጽንኦት ላይ ማተኮሩም አያስገርምም! መጽሐፉን የጻፈው እንደ ጠንቃቃ ታሪክ ጸሐፊ እያሰበና እንደ አፍቃሪ ሐኪም እየራራ ነበር።

የሉቃስ ወንጌል የተጻፈው ለቴዎፍሎስ ነበር፤ ቴዎፍሎስ «የእግዚአብሔር ፍቅር» የሚል ፍች ሲኖረው፥ ምናልባትም በክርስቶስ በማመኑ በእምነቱ ለመጽናት ተጨማሪ ማብራሪያ ያስፈለገው የሮም ባለሥልጣን ይሆናል። እንዲሁም ቴዎፍሎስ የክርስትናን መልእክት የተማረ እውነት ፈላጊ ሊሆን ይችላል፤ ይህንንም ልንል የቻልነው በቁጥሩ 4 «ስለተማርኸው» የሚለው

ሐረግ «የክርስትናን መሠረታዊ ትምህርቶች የሚማር» የሚል ትርጉም ስለሚሰጥ ነው።

የክርስቶስ ሕይወትና መልእክቱ እጅግ አስፈላጊዎች በመሆናቸው፥ በዚህ ጊዜ አያሌ መጻሕፍት ተጽፈው ነበር፤ ይህም ሆኖ፥ በተጻፉት መጻሕፍት ወስጥ የሚገኙ ነገሮች ሁሉ ሊታመኑ የሚችሉ አልነበሩም። ሉቃስ ወንጌሉን የጻፈው አንባቢዎቹ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፥ አገልግሎትና መልእክት ትክክለኛና በቅደም ተከተል የተዘጋጀ ታሪክ እንዲያገኙ ነበር። ሉቃስ መጽሐፉን ያዘጋጀው ያሰባሰባቸውን ጽሑፎች በጥንቃቄ በመመርመር፥ የዓይን ምስክሮችን በመጠየቅና የቃሉን አገልጋዮች በማዳመጥ ነበር ። ከዚህም ሁሉ በላይ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት በሥራው ሁሉ አብሮት ነበር። «ከመጀመሪያው» (በግሪኩ ኤኖተን) የሚለው ቃል በዮሐንስ 3፡31 እና 19፡11 እንዳለው «ከላይ» ተብሎ ሊተረጐም የሚችል ሲሆን፥ የሚናገረውም ሉቃስ በጻፈው መልእክት ላይ እስትንፋሰ–እግዚአብሔር ማረፉን ነው።

ሉቃስ በመጽሐፉ የመጀመሪያ ምዕራፍ፥ የእግዚአብሔር አስደናቂ ዜና ወደ ተለያዩ ሰዎች እንዴት እንደመጣና እነርሱም ምን ዓይነት ምላሽ እንደ ሰጡ ይነግረናል። በዚህም መሠረት አራት የተለያዩ ምላሾች ተገልጸዋል።

## 1. አለማመን (1፡5–25)።

ይህ በትክክል ለእስራኤል ሕዝብ የጽልመት ጉም ያጠላበት ጊዜ ነበር። ነቢዩ ሚልክያስ ስለ ኤልያስ መምጣት ከተነበየበት ጊዜ አንሥቶ (ሚል. 4፡5–6)፥ ሕዝቡ ለ400 ዓመታት ከእግዚአብሔር ዘንድ ምንም ዓይነት የትንቢት ቃል አልሰማም። መንፈሳውያን መሪዎች በወግ ሰንሰለት የተጠፈሩ ሲሆን፥ አንዳንድ ጊዜም ነውር ይታይባቸው ነበር፤ ንጉሣቸው የነበረው ታላቁ ሄሮድስ ደግሞ የለየለት አምባገነን ነበር። ዘጠኝ (እንደ አንዳንዶቹ አባባል አሥር) ሚስቶች የነበሩት ይኸው ሰው አንዱን ይህ ነው ለማይባል ምክንያት ገድሏታል። ይሁንና፥ ዘመኑ ምንም የጨለመ ቢሆን እግዚአብሔር ሁልጊዜም የተሰጡና የሚታዘዙ ሕዝቦች አሉት።

<u>ታማኝ ካህን</u> (ቁጥር 5–7)። የስሙ ትርጓሜ «ያህዌ አስታውሶአል» የሚለው ዘካርያስና «እግዚአብሔር መሐላዬ ነው» የሚል ፍቺ ባዘለ ስያሜ የምትጠራው ኤልሳቤጥ ከካህናት ዘር የመጡ መንፈሳውያን ባለትዳሮች ነበሩ። ካህናት በሃያ አራት ተራዎች የተመደቡ ሲሆን (1ኛ

ዜና 24)፥ እያንዳንዱ ካህን በመቅደስ ውስጥ በዓመት ለሁለት ሳምንታት ያገለግል ነበር። ዙሪያቸውን ካጣበበው እግዚአብሔርን ያለመፍራት ባሻገር፥ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ በታማኝነት የእግዚአብሔርን ቃል ይታዘዙና ያለ ነውር ይመላለሱ ነበር።

ብቸኛው ኀዘናቸው ልጅ አለመውለዳቸው ሲሆን፥ ሁልጊዜም በዚህ ጉዳይ ላይ ይጸልዩ ነበር። ግን እግዚአብሔር ጸሎታቸውን በመስማት ካህን ሳይሆን ነቢይ እንደሚሰጣቸው አልተረዱም። ልጃቸውም ቢሆን የመጭው ንጉሥ አዋጅ ተናጋሪ ስለሚሆን ተራ ነቢይ አይሆንም ነበር።

<u>ፈሪ ካህን</u> (ቁጥር 8-17)። በአገልግሎት ተግባር ላይ የነበሩ ካህናት ድርሻቸውን ለመለየት ዕጣ ሲጥሉ፥ ዘካርያስ በቅዱስ ስፍራ ዕጣን የማጠን ሥራ ደረሰው። ይህ ለአንድ ካህን በሕይወት ዘመኑ አንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጠው ዕድል በመሆኑ ትልቅ ክብር ነበር። ዕጣን ዘወትር ከጠዋቱ መሥዋዕት በፊትና ቀትር ወደ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ከሚቀርበው የምሽት መሥዋዕት በኋላ ይታጠን ነበር። ምናልባት ለዘካርያስ የተሰጠው የምሽቱ መሥዋዕት ይሆናል።

ምናልባት እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ሰዎች የዕለት ተግባራቸውን ለማከናወን በሚጣደፉበት ወቅት እንደሚጠራቸውና እንደሚናገራቸው አስተውለህ ይሆናል። እግዚአብሔር ሲጠራቸው ሙሴና ዳዊት በጐችን ይጠብቁ ነበር። ጌዴዎን እህል ይወቃ ነበር። ጴጥሮስና ባልደረቦቹም ኢየሱስ በጠራቸው ጊዜ መረባቸውን ይጠግኑ ነበር። ሞተር ሳይሠራ ሲቀር መኪና ማሽከርከር አይቻልም። እንደዚሁም፥ እግዚአብሔር ሊመራን የሚጀምረው ሥራ ላይ ስንሆን ነው።

ሉቃስ በወንጌሉ ውስጥ መላእክትን ሃያ ሦስት ጊዜ ጠቅሶአል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስማቸው የተጠቀሱት ሁለት ብቻ ማለትም ሚካኤል (ዳን. 10፡13፥21፤12፡1፤ ይሁዳ ቁጥር 9 እና ራእይ 12፡7) እና ገብርኤል (ዳን. 8፡16፤ 9፡21፤ ሉቃ. 1፡19፥26) ሲሆኑ፥ እጅግ በርካታ መላእክት አሉ (ራእይ 5፡11)። ገብርኤል ወደ መሠዊያው ሲቀርብ ዘካርያስ ደነገጠ፤ ይህም የመልአክ መምጣት መለኮታዊ ፍርድን ያነገበ ሊሆን ስለሚችል ነው።

«አትፍራ!» የሚለው ቃል በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅሶአል (1፡13፥30፤ 2፡10፤ 5፡10፤ 8፡50፤ 12፡7፥32)። ዘካርያስ እርሱና ባሌቤቱ ኤልሳቤጥ ልጅ እንደሚወልዱ ሲረዳ ምን ያህል እንደ ተደሰተ በምናብህ ለመቃኘት ሞክር! «ደስታ» ሌላው በሉቃስ ወንጌል ውስጥ

የሚገኝ ዐቢይ አሳብ ሲሆን፥ ቢያንስ አሥራ ዘጠኝ ጊዜ ያህል ተጠቅሶአል። መልካም የምሥራች ደስታን ያስከትላል።

መልአኩ ገብርኤል ዘካርያስ ልጁን ዮሐንስ («ያህዌ ቸር ነው») ብሎ እንዲጠራውና ልጁም በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ናዝራዊ ይሆን ዘንድ ለእግዚአብሔር እንዲሰጠው አዘዘው (ዘኁል. 6፡1–21)። ዮሐንስ ከመወለዱ አስቀድሞ በመንፈስ ቅዱስ ይሞላና (ቁጥር 41) የእግዚአብሔርን ልጅ ለእስራኤል ሕዝብ ለማስተዋወቅ ነቢይ ይሆን ነበር (ዮሐ. 1፡15–34)። ኢሳይያስ እንደተነበየው (ኢሳ. 40፡1–5)፥ እግዚአብሔር አያሌ ሰዎችን ወደ ራሱ ለመመለስ የዮሐንስን አገልግሎት ይጠቀም ነበር።

<u>እምነተ–ቢስ ካህን</u> (ቁጥር 18–22)። የመልአኩ መገኘትና የእግዚአብሔር ቃል መታወጅ የዘካርያስን እምነት ያጠናክረዋል ብለህ ታስብ ይሆናል፤ ግን ይህ ሊሆን አልቻለም። በእምነት ወደ እግዚአብሔር ከማየት ይልቅ፥ ካህኑ ወደ ራሱና ወደ ባለቤቱ በመመልከት የልጁን መወለድ የማይቻል ጉዳይ አድርጎ ደመደመ። ምናልባትም ከእግዚአብሔር በምልክትነት ከተሰጠው ከመልአክተኛው ገብርኤል ቃል የበለጠና ተጨማሪ ማረጋገጫ ፈለገ።

ይህ በመሠረቱ አለማመን ነው፤ አለማመን ደግሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም። ዘካርያስ እግዚአብሔር የሰጠውን ቃል ለመፈጸም ስለመቻሉ እየተጠራጠረ ነበር። እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም ለአብርሃምና ለሣራ ያደረገላቸውን ዘንግቶ ይሆን? (ዘፍጥ. 18፡9–15፤ ሮሜ 4፡18–25)። ወይስ ሥጋዊ ውሱንነቱ እግዚአብሔርን ያቅበዋል ብሎ አስቦ ነው? ይሁንና፥ ዘካርያስ ላይ ብዙ ከመፍረዳችን በፊት ራሳችንን በመመርመር የእምነታችንን ጥንካሬ ልንመዝን ይገባል።

እምነት በረከትን ሲያስከትል አለማመን ደግሞ ፍርድን ያመጣል፤ ስለሆነም፥ ዘካርያስ የተባለው ቃል እስኪፈጸም ድረስ ድዳ (ምናልባትም ደንቆሮ ቁጥር 62) ሆኖ እንዲቆይ ተፈረደበት። «አመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ» (2ኛ ቆሮ. 4፡13)። ዘካርያስ ስላላመነ ሊናገር አልቻለም። ዘካርያስ ከቅዱሱ ስፍራ ሲወርድ ለሕዝቡ ካህናዊ ቡራኬ (ዘኁል. 6፡22–27) ለመስጠትም ሆነ ያየውን ነገር ለመናገር አልቻለም። እግዚአብሔር ለሚቀጥሉት ዘጠኝ ወራት አብሮት የሚኖረውን በጣም የተሰወረ «ምልክት» ሰጥቶት ነበር።

<u>የታደለ ካህን</u> (ቁጥር 23–25)። ዘካርያስ በደረሰበት የአካል ጉዳት ሳቢያ ብቻ ሳይሆን በመደነቁ ጭምር የአገልግሎት ሳምንቱን ለመፈጸም ሳይቸገር አልቀረም። ወደሚኖርበት «ወደ ተራራማው አገር»

ተመልሶ (ቁጥር 39) መልካሙን የምሥራች ለባለቤቱ ለመናገር ቻኩሎ ነበር።

እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል በመጠበቁ ኤልሳቤጥ በስተርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀነሰች። ለእግዚአብሔር የሚያቅተው ነገር የለም (ኤር. 32:17)። እግዚአብሔርን በምታመሰግንበት ወቅት የሰዎች አድናቆትና ጉጉት ከብዙዎች እይታ ተሰውራ እንድትቆይ አደረጋት። ልጅ መውለዱ ብቻ ሳይሆን፥ የምትወልደው ልጅ መሢሑ እየመጣ እንደሆነ በመረጃነት የሚያረጋግጥ ነበር። እውነትም እነዚህ አስደናቂ ጊዜያት ነበሩ።

## 2. እምነት (1:26–38)።

ኤልሳቤጥ በፀነሰች በስድስተኛው ወር ገብርኤል ሁለተኛውን ልጅ የመውለድ ማስታወቂያ ይዞ መጣ፤ በዚህ ጊዜ መልእክቱ የመጣው በናዝሬት ለምትኖርና ማርያም ለምትባል ልጃገረድ ነበር። ለመልአኩ በተሰጡት ሥራዎች መካከል ልዩነት ነበር፤ አንድ ሽማግሌና አንዲት ወጣት ሴት፥ ካህንና የንጉሡ የዳዊት ዝሪያ፥ ቤተ መቅደስና ተራ የመኖሪያ ቤት፥ ኢየሩሳሌምና ናዝሬት፥ አለማመንና ማመን ይነጻጸሩ ነበር።

የይሁዳ ሰዎች በገሊላ የሚኖሩ አይሁዶች ከአሕዛብ ጋር ካላቸው ግንኙነት ሳቢያ የአይሁድ ሕግ የሚጠብቅባቸውን እንደማያሟሉ በመግለጽ ይጠሉአቸው ነበር (ማቴ. 4:15)። በተለይም የናዝሬትን ነዋሪዎች አብዝተው ይጠሉዋቸው ነበር (ዮሐ. 1:45–46)። ይህም ሆኖ፥ እግዚአብሔር በጸጋው በዚህ በተናቀው የገሊላው ናዝሬት ትኖር የነበረችው ልጃገረድ ተስፋ የተሰጠው መሢሕ እናት እንድትሆን መረጠ!

ማርያምን በተመለከተ ሰዎች ከሁለት አከራሪ አቅጣጫዎች አንዱን ወደ መምረጡ ያዘነብላሉ። አንድም ማርያምን እጅግ በማጉላት ለኢየሱስ ሁለተኛውን ስፍራ ይሰጣሉ (ቁጥር 32) ወይም ጭራሹኑ ገለል በማድረግ የሚገባትን ደረጃ ከመስጠት ይታቀባሉ (ቁጥር 48)። ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ «የጌታዬ እናት» ብላታለች (ቁጥር 43)፤ ይህም ማርያምን ለማክበር በቂ ምክንያት ነው።

ስለ ማርያም ምን እናውቃለን? ማርያም ከይሁዳ ነገድ፥ ከዳዊት ትውልድ የሆነች አይሁዳዊት ድንግል ነበረች (ኢሳ. 7:14)። በናዝሬት ከተማ በአናጺነት ሙያ ለሚተዳደር ዮሴፍ ለተባለ ሰው የታጨች ስትሆን (ማቴ. 13:55)፥ ሁለቱም ድሆች የነበሩ ይመስላል (ሉቃ.

2:24፤ ዘሌ. 12፡8)። በዚያን ጊዜ ለአይሁዶች ትጭጭት የጋብቻን ያህል የጠነከረ ትስስር በመሆኑ መለያየት የሚቻለው በፍቺ ብቻ ነበር። እንዲያውም ጋብቻው ከመፈጸሙ በፊት ወንድየውና ሴትዮዋ «ባል» እና «ሚስት» ተብለው ይጠሩ ነበር (ማቴ. 1፡19ን ከሉቃስ 2፡5 ጋር አመሳክር)። የአይሁድ ልጃገረዶች የሚያገቡት ገና በትንሽነታቸው ስለነበር፥ መልአኩ በታያት ጊዜ ማርያም ገና በአሥራ ሦስትና በሃያ ዓመታት መካከል የምትገኝ ወጣት ሳትሆን አትቀርም።

<u>የማርያም መደነቅ</u> (ቁጥር 26–33)። የገብርኤልን ሰላምታ አጢነህ ስትመለከት፥ ማርያም ለምን ግራ እንደተጋባችና እንደፈራች ልትረዳ ትችላለህ፤ «ደስ ይበልሽ፥ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው» አላት። መልአኩ ሰላምታ ሊሰጣት የመጣው ለምንድን ነው? ጸጋ የሞላባት በምን መንገድ ነበር? እግዚአብሔር ከእርሷ ጋር የሆነውስ እንዴት ይሆን?

የማርያም ምላሽ በእግዚአብሔር ፊት ትሑትና እውነተኛ እንደነበረች ያሳያል። ከቶውንም መልአክ እንድምትመለከትና ከሰማይ ልዩ ጸጋዎችን እንደምታገኝ አልጠበቀችም። እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች እንዲፈጸሙላት የሚያደርግ ምንም የተለየ ነገር አልነበራትም። አንዳንድ የሥነ–መለኮት አዋቂዎች እንደሚሉት፥ ማርያም ከሌሎች አይሁዳውያን ልጃገረዶች የተለየች ብትሆን ኖሮ፥ «መልካም፥ ጊዜው እንግዲህ ደርሶአል! እስካሁንም ስጠብቅህ ቆይቻለሁ!» ትል ነበር። በፍጹም! ሁሉም ነገር ለእርሷ አዲስና አስደናቂ ዱብዕዳ ነበር።

ከዚያም ገብርኤል መልካሙን ዜና አበሰራት፤ ይኸውም ኢየሱስ («ያህዌ ደኅንነት ነው» ማቴ. 1፡21) ብላ የምትሰይመውን የተስፋ ቃል የተገባለት መሢሕ እንደምትወልድ ነበር። ገብርኤል የኢየሱስን አምላክነትና ሰብአዊነት እንደመሰከረ ልብ በል። የማርያም ልጅ እንደመሆኑ ሰው ነበር፤ የልዑል ልጅ በመሆኑ ደግሞ (ቁጥር 32) የእግዚአብሔር ልጅ ነበር (ቁጥር 35)። «ሕፃን ተወልዶልናልና [ሰብአናው]፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና [መለኮታዊነቱ]...» (ኢሳ. 9፡6)። ትኩረት የተሰጠው በልጁ ታላቅነት ላይ እንጂ፥ በእናቱ ታላቅነት ላይ አይደለም (ከ1፡15 ጋር አመሳክር)።

እንዲሁም፥ ንጉሥ በመሆን የዳዊትን ዙፋን ይወርስና ለዘላለም በእስራኤል ላይ ይነግሣል! ገብርኤል ከቁጥር 30–31 የተናገረውን ቃል በቃል ከፈታን፥ በቁጥር 32–33 የተናገረውንም ደግሞ ቃል በቃል ልንፈታው ይገባል። በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን (2ኛ ሳሙ. 7) እና ለእስራኤል ሕዝብ የሰጠውን

የመንግሥት የተስፋ ቃሎች እያመለከተ ነበር (ኢሳ. 9፡1-7፤11-12፤61፤66፤ ኤር. 33)።

ኢየሱስ ወደ ዓለም የመጣው የዓለም አዳኝ ለመሆን ነበር፤ ከዚህም በተጨማሪ፥ አመጣጡ እግዚአብሔር ለአይሁዳውያን አባቶች የገባላቸውን የተስፋ ቃሎች ለመፈጸም ሲል ነው (ሮሜ. 15፡14)። ዛሬ ኢየሱስ በዳዊት ዙፋን ላይ ሳይሆን በሰማያዊ ዙፋን ላይ ተቀምጦአል (የሐዋ. 2፡29-36)። አንድ ቀን ኢየሱስ ተመልሶ ይመጣና በምድር ላይ የጽድቅ መንግሥቱን ይመሠርታል፤ በዚያን ጊዜም እነዚህ የተስፋ ቃሎች ይፈጸማሉ።

<u>የማርያም መሰጠት</u> (ቁጥር 34-48)። ማርያም የሚሆነውን ነገር ብታውቅም እንዴት እንደሚፈጸም ግን አታውቅም ነበር። በቁጥር 34 ላይ ያነሣችው ጥያቄ አለማመኗን የሚያሳይ ሳይሆን እምነቷን የሚገልጽ ነበር። የተስፋ ቃሉን ብታውቅም እንዴት እንደሚፈጸም አልገባትም ነበር። አንዲት ልጃገረድ እንዴት ከወንድ ጋር ሳትገናኝ ልትወልድ ትችላለች?

በመጀመሪያ፥ ይህ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚፈጸም ተአምር እንደሚሆን ገብርኤል አብራርቷል። ምንም እንኳ ኢየሱስ በሰዎች የዮሴፍ ልጅ ተብሎ የሚጠራ ቢሆንም (ሉቃ. 3፡23፤4፡22፤ ዮሐ. 1፡45፤6፡42)፥ እውነኛዋ ዮሴፍ የልጁ አባት አይሆንም ነበር። አንዳንድ ሰዎች ማርያም ለዮሴፍ ታማኝ ባለመሆኗ ኢየሱስ «በዝሙት እንደተወለደ» ሊያስቡ ይችላሉ (ዮሐ. 8፡41)። ይህ ማርያም በሕይወት ዘመኗ ሁሉ እየሰማች ለመኖር የተገደደችው አሰቃቂ አሉባልታ አካል ነበር (ሉቃ. 2፡35)።

ገብርኤል ሕፃኑ «ቅዱስ» እንደሚሆንና የሰውን ኃጢአተኛ ሥጋዊ ተፈጥሮ እንደማይጋራ በጥንቃቄ አመልክቶአል። ኢየሱስ ኃጢአት አላወቀም (2ኛ ቆሮ. 5፡21)፤ ምንም ኃጢአት አልፈጸመም (1ኛ ጴጥ. 2፡22)፤ በእርሱም ኃጢአት የለም (1ኛ ዮሐ. 3፡5)። ሰውነቱ የተዘጋጀለት ማርያምን «በጸለለው» የእግዚአብሔር መንፈስ አማካኝነት ነበር (ዕብ. 10፡5)። በዘፀአት 40፡35 በአይሁድ የመገናኛ ድንኳንና መቅደስ ውስጥ በቅድስተ ቅዱሳኑ የእግዚአብሔርን መገኘት በማመልከት «ሞላ» ተብሎ የተተረጐመው ይኸው ተመሳሳይ ቃል ነው። የማርያም ማኅፀን ለእግዚአብሔር ልጅ ቅድስተ ቅዱሳን ሆነ!

መልአኩ መልእክቱን የደመደመው ለማርያም የማጽናኛ ቃል በመስጠት ነበር፤ ይኸውም በዕድሜ የገፋችው ዘመዷ ኤልሳቤጥ ልጅ መውለዷ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር እንደሌለ፥ እንዲሁም

የይስሐቅን መወለድ ባወጀ ጊዜ ለአብርሃምም ተመሳሳይ ቃል ሰጥቶት ነበር (ዘፍጥ. 18፡14)። እምላካችን ማንኛውንም ነገር ሊያደርግ መቻሉ ኢዮብን (42፡2)፥ ኤርምያስን (32፡17) እና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ጨምሮ በብዙዎች ተመስክሮአል (ማቴ. 19፡26)። በተለይ ይህንን ቃል በ1901 ከታተመው የአሜሪካን ስታንዳርድ እትም መጽሐፍ ቅዱስ ማንበቡ ያረካኛል፤ ይህ እትም «ማንኛውም የእግዚአብሔር ቃል ኃይል ያጣ ሊሆን አይችልም» ይላል። እግዚአብሔር በቃሉ ኃይል አማካኝነት ዓላማዎቹን ይፈጽማል [መዝ. (33)፡9]።

የማርያም የእምነት ምላሽ እንደ ታዛዥ ባርያ ራሷን ለእግዚአብሔር መስጠት ነበር። የእግዚአብሔር ጸጋ ስለተሰጣት (ቁጥር 30) እና የእግዚአብሔርን ቃል ስላመነች፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም መንፈስ ቅዱስ ሊጠቀምባት ይችል ነበር። እጅግ ዝቅተኛ የሆነች የሴት ደንገጡር ማርያም በእግዚአብሔር ምን ያህል እንደተደገፈች ታሳያለች። ሰውነቷን (ቁጥር 38)፥ ነፍሷን (ቁጥር 46)፥ ብሎም መንፈሷን (ቁጥር 47) ሁሉ በማስገዛት ለጌታ ሙሉ ለሙሉ ራሷን ሰጥታለች። ልንከተላት የሚገባን ምንኛ ግሩም ምሳሌ ነች! (ሮሜ 12፡1-2)።

### 3. ደስታ (1፡39-56)።

ማርያም የልጅ እናት እንደምትሆንና ዘመዱ ኤልሳቤጥም በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ እንደምትወልድ በመረዳቷ፥ አብረው ደስ ይሰኙ ዘንድ ወደ ኤልሳቤጥ ዘንድ መሄድ ፈለገች። ሦስት ሰዎች በጌታ ደስ ሲሰኙ የምንመለከትበት ይህ ክፍል በዋናነት ስለ ደስታ ይናገራል።

መጀመሪያው፥ የኤልሳቤጥ ደስታ ነው (ቁጥር 39-45)። ማርያም ወደ ቤቷ ስትገባ ኤልሳቤጥ የሰላምታዋን ድምፅ ሰማች፤ በመንፈስ ቅዱስም ተሞልታ ማርያም ለምን እንደመጣች ከጌታ ተረዳች። በዚህ ጊዜ አፏን የሞላው አንድ ቃል «የተባረክሽ» የሚል ነበር። ኤልሳቤጥ ማርያምን «ከሴቶች በላይ የተባረክሽ» እንዳላለቻትና ዳሩ ግን «ከሴቶች መካከል የተባረክሽ» እንዳለቻት ልብ በል፤ ይህም በትክክል እውነት ነው። ለማርያም እግዚአብሔር ብቻ ሊቀበል የሚገባውን የአምልኮት ክብር ባንሰጣትም፥ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ያላትን ስፍራ ልናሳንስ አይገባም።

ኤልሳቤጥ ያገነነችው ነገር ቢኖር የማርያምን እምነት ነበር፤ «ያመነች ብፅዕት ናት» (ቁጥር 45)። «ጸጋው በእምነት...» አድኖናል (ኤፌ. 2፡8-9)። ማርያም የእግዚአብሔርን ቃል ስላመነች የእግዚአብሔርን ኃይል ተቀበለች።

ሁለተኛ፥ በጊዜው የማይታየው ዮሐንስም ደስ ተሰኝቶአል (ቁጥር 41 እና 44)። ምናልባትም መልአኩ እንደተናገረው በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው በዚህ ጊዜ ሳይሆን አይቀርም (ቁጥር 15)። ዮሐንስ በምድራዊ አገልግሎቱ እንዳደረገው ሁሉ ሳይወለድም በፊት በኢየሱስ ክርስቶስ ደስ ተሰኝቶአል (ዮሐ. 3፡29-30)። ካደገ በኋላ መጥምቁ ዮሐንስ ተብሎ ሲታወቅ፥ መሢሑን ለአይሁድ ሕዝብ የማስተዋወቅ ታላቅ ዕድል አግኝቷል።

ሦስተኛ፥ የማርያምም ደስታ ነበር (ቁጥር 45-56)፤ ይህም ደስታ በምስጋና መዝሙር ድምጿን ከፍ አድርጋ እንድታሰማ አድርጓታል። በሕይወታችን የመንፈስ ቅዱስሙላት በደስታ ወደማመስገኑ ሊመራን ይገባል (ኤፌ. 5፡18-20)፤ የቃሉም ሙላት እንዲሁ (ቈላ.3፡16-17)። የማርያም መዝሙር ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት፥ በተለይም ከመዝሙረ ዳዊትና በ1ኛ ሳሙኤል 2፡1-10 ከሚገኘው የሐና ጸሎት የተወሰዱትን ጥቅሶች ያካትታል። ማርያም የእግዚአብሔርን ቃል በልቧ ሸሽጋ ኖራ ወደ መዝሙር ለወጠችው።

ይህ መዝሙር በቁጥር 46 ላይ ከሚገኘው የላቲን አትም ተወስዶ «ዘ ማግኒፍካት» (አከብሮት፥ ከፍ ከፍ ማድረግ) ተብሎ ይጠራል። የማርያም ትልቅ መሻት ጌታን እንጂ ራሷን ከፍ ከፍ ማድረግ አልነበረም። ማርያም እግዚአብሔር ለሦስት ተቀባዮች ያደረጋቸውን ነገሮች ዘርዝራለች።

<u>እግዚአብሔር ለማርያም ያደረገው</u> (ቁጥር 46-49)። በመጀመሪያ ደረጃ፥ እግዚአብሔር ማርያምን አድኖአታል (ቁጥር 47) «መድኃኒቴ»)፤ ይህም ማርያም እንደማንኛውም ሰው ኃጢአተኛ እንደነበረችና ለዘላለማዊ ደኅንነቷ በጌታ ማመን እንዳስፈለጋት ያመለክታል። ማዳን ብቻም አይደለም እግዚአብሔር የመሢሑ እናት እንድትሆንም መርጦአታል (ቁጥር 48)። «ውርደቷን ተመልክቶአል» ይህም እንዳስታወሳትና በጸጋው እንደተመለከታት ያሳያል። ሌሎችም ሊመረጡ ይችሉ የነበሩ ሴቶች እንዳልታጡ ጥርጥር የለውም፤ እግዚአብሔር ግን እርሷን መረጣት! እውነትም እግዚአብሔር ጸጋውን አብዝቶላታል (1ኛ ቆሮ. 1፡26-28 ተመልከት)።

እግዚአብሔር ማርያምን ማስታወስ ብቻ ሳይሆን፥ ለእርሷ ወኪል ሆኖ በመቆም ታላቅ ነገርም አድርጎላታል (ቁጥር 49)። ማርያም «ታላቅ ነገር አደረገልኝ!» እያለች ለመዘመር አትቸገርም ነበር (ሉቃ. 8፡39፤ 1ኛ ሳሙ. 12፡24፤ 2ኛ ሳሙ.7፡21-23፤ መዝ. [126]፡2-3)። ማርያም እግዚአብሔርን ስላመነችና ለፈቃዱ ራሷን ስለ ሰጠች፥

በሕይወቷ ተአምር ከመሥራቱም በላይ አዳኙን ወደ ዓለም ለማምጣት ተጠቅሞባታል።

<u>እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገው</u> (ቁጥር 50–53)። ማርያም ከመዝሙሯ ሁለተኛ ቁጥር ውስጥ ከትውልድ ትውልድ እግዚአብሔርን የሚፈሩትን ሕዝቦቹን ሁሉ አካትታለች። ሁላችንም ምሕረቱንና እገዛውን ተቀብለናል። ማርያም እግዚአብሔር ምሕረቱን ያሳያቸውን ሁለት የተወሰኑ ቡድኖች ጠቅሳለች፤ እነዚህም፥ ትሑታን (ቁጥር 52) እና የተራቡ (ቁጥር 53) ናቸው።

ፍትሕንና ሕዝባዊ መብቶችን በተመለከተ፥ በዘመኑ የነበሩ ተራ ሰዎች ምስኪኖች ነበሩ ማለት ይቻላል። በአብዛኛው የተራቡ፥ የተረገጡና ተስፋ የቆረጡ ሲሆኑ (ሉቃ. 4፡16–19)፥ መንግሥቱን የሚዋጉበት መንገድ አላገኙም። አክራሪ አይሁዳውያን የሚገኙበት የአድመኞች ድርጅት የሮምን መንግሥት ለመቃወም የዓመፅ እርምጃ ቢወስድም፥ ውጤቱ ያው በራሳቸው ላይ ሁኔታውን ማባባስ ነበር።

ማርያም ጌታ ነገሮችን ሁሉ ሲገለብጥ ተመለከተች፤ ደካሞች ብርቱዎችን ከዙፋኖቻቸው ሲያፈናቅሉ፥ ትሑታን ኩራተኞችን ሲበትኑ፥ የማንነት መታወቂያ ያልነበራቸው ከፍ ከፍ ሲሉ፥ የተራቡት ሲጠግቡና ሀብታሞች ለድህነት ሲዳረጉ አየች። የእግዚአብሔር ጸጋ የሚሠራው ከዚህ ዓለም ሥርዓት አሳብና መንገድ በራቀ ስልት ነው (1ኛ ቆሮ. 1፡26–28)። ቤተ ክርስቲያን በዳዊት ዙሪያ የተሰበሰቡትን የሰዎች ቡድን ትመስላለች (1ኛ ሳሙ. 22፡2)።

<u>እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገው</u> (ቁጥር 54–55)። «ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና» (ማቴ. 1፡21)። ከእስራኤል ቀውጢ ሁኔታ ባሻገር፥ ሕዝቡ አሁንም የእግዚአብሔር ባሪያ በመሆኑ እግዚአብሔር ዓላማዎቹን እንዲፈጽም ይረዳው ነበር። እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጐን ነበር። ምሕረቱን ያስታውስና የተስፋ ቃሎቹን ይጠብቅ ነበር (መዝ. (98)፡1–3፤ በተጨማሪም፥ ዘፍጥ. 12፡1–3፤ 17፡19፤ 22፡18፤ 26፤4፤ 28፡14)። እስራኤል ባይሆን ኖሮ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ተወልዶ ወደ ዓለም ሊመጣ አይችልም ነበር።

ማርያም ዮሐንስ እስኪወለድ ድረስ ከኤልሳቤጥ ዘንድ ሰነበተችና ወደ ናዝሬት ተመለሰች። በዚህ ጊዜ ነፍሰ–ጡርነቷ እንደታወቀና ሰዎችም አሽሙራቸውን እንደጀመሩ አይጠረጠርም። ለሦስት ወራት ከቤት ርቃ የቆየች በመሆኑ ለምን እንዲህ ቸኩላ እንደሄደች ሰዎች እርስ በርሳቸው ሳይጠያየቁ አልቀሩም። በዚህ ጊዜ ነበር እግዚአብሔር

ለዮሴፍ መልካም ዜና ያበሰረለትና ምን ሊያደረግ እንደሚገባው የነገረው (ማቴ. 1፡18–25)።

## 4. ምስጋና (1፡57–80)።

የእግዚአብሔር በረከት በዘካርያስና በኤልሳቤጥ ላይ ተትረፍርፎ ነበር። እንደተናገረው ወንድ ልጅ ሰጣቸውና፥ እነርሱም እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው «ዮሐንስ» ብለው ሰየሙት። አይሁዶች ልጆችን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚመጡ ስጦታዎችና ከጌታ እንደሚሰጥ ርስት ይመለከቱ ነበር [መዝ. (127)፡3–5 እና (128)፡1–3]፤ ይህም ትክክለኛ ግንዛቤ ነው። እስራኤላውያን ልጆቻቸውን ከማኅፀን በማጨናገፍ ወይም በማግለል የአረማዊ ጐረቤቶቻቸውን ልማዶች አይከተሉም ነበር። በአሜሪካ ብቻ በየዓመቱ 1,500,000 ሕፃናት በውርጃ አማካኝነት በእናቶቻቸው ማኅፀን እንደሚጨናገፉ ስትመለከት፥ ከእግዚአብሔር ሕግጋት ምን ያህል እንደራቅን ልትገነዘብ ትችላለህ።

ዶክተር ኢ. ቲ. ሱሊቫን ሲናገሩ፥ «በዓለም ላይ ከሁሉም የሚልቁ ኃይላት ርዕደ–ምድሮችና መብረቆች ሳይሆኑ፥ ሕፃናት ናቸው» ብለዋል።

በተለምዶ ወንድ ልጅ የሚሰየመው በአባቱ ወይም በቤተሰቡ ውስጥ በሚገኝ ሌላ ሰው ስም ነበር፤ ስለሆነም፥ ኤልሳቤጥ «ዮሐንስ» በሚለው ስም ላይ ስታተኩር ዘመዶቻቸውና ጐረቤቶቻቸው ደነገጡ። በኋላም ዘካርያስ «ስሙ ዮሐንስ ነው» ሲል በጽላት ላይ በመጻፉ ችግሩ ተቃለለ። ወዲያው እግዚአብሔር የሽማግሌውን ካህን አፍ ከፈተለትና የኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መምጣት ምን እንደሆነ የሚያሳዩትን አራት ውብ ምሳሌዎች ያካተተ መዝሙር ዘመረ።

<u>የወኅኒ ቤት በር መከፈት</u> (ቁጥር 68)። «ቤዛ» የሚለው ቃል «ዋጋ በመክፈል ነፃ ማውጣት» ማለት ነው። ይህም የእስረኛን መለቀቅ ወይም የባሪያን ነፃ መውጣት ሊያመለክት ይችላል። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው ምርኮኞችን ነፃ ሊያወጣ (ሉቃ. 4፡18)፥ በኃጢአትና በሞት ታስረው ላሉት ደኅንነትን ሊሰጥ ነው። በመሠረቱ፥ እኛ ራሳችንን ነፃ ለማድረግ አንችልም፤ ለቤዛችን የሚያስፈልገውን ዋጋ ሊከፍል የሚችለው ክርስቶስ ብቻ ነው (ኤፌ. 1፡7፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡18–21)።

የጦርነቱ ድል መነሣት (ቁጥር 69–75)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቀንድ ኃይልንና ድልን ያመለክታል (1ኛ ነገሥት 22፡11፤ መዝ. (89)፤ 17፥24።) በዚህ ስፍራ የተመለከተው ገለጻ በምርኮኛነት ሊወሰድ ከተቃረበ በኋላ አጋዥ በመድረሱ ጠላቱን ያሸነፈው ሠራዊት ነው። በቀደመው ገለጻ፥ ምርኮኞች ነፃ ተለቀዋል፤ በዚህ ገለጻ ግን ጠላት ስለተሸነፈ ከእንግዲህ ሌሎችን እስረኞች በምርኮኛነት አይወስድም። ይህም ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሙሉ ድል ማለት ነው።

«ደኅንነት» የሚለው ቃል (ቁጥር 69–71) «ጤናማነት» የሚል ፍች አለው። ምርኮኞች በጣም የደከሙ ቢሆን እንኳ ተቤዥው መንፈሳዊ ጤንነት ያመጣል። ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝህ አድርገህ ስታምን፥ ከሰይጣን ኃይል ነፃ ወጥተህ ይቅር በመባልና በመቤዠት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ትገባለህ (ቈላ. 1፡12–14)።

ተቤዥው ከየት መጣ? የመጣው ከዳዊት ቤት ሲሆን (ቁጥር 69)፥ እርሱም ራሱ ታላቅ ድል–ነሺ ነበር። እግዚአብሔር አዳኙ የሚመጣ አይሁዳዊ (ዘፍጥ. 12፡1–3) ከይሁዳ ነገድ (ዘፍጥ. 49፡10)፥ ከዳዊት ቤተሰብ (2ኛ ሳሙ. 7፡12–16) ሆኖ፥ በዳዊት ከተማ በቤተልሔም እንደሚወለድ (ሚክ. 5፡2) አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። ሁለቱም ማርያም (1፡27) እና ዮሴፍ (ማቴ. 1፡20) ከዳዊት የዘር ሐረግ ናቸው። የተቤዥው መምጣት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ባደረጋቸው ቃል ኪዳኖች ውስጥ የሚገኝ ሲሆን (ቁጥር 72)፥ ይህም በነቢያት የተነገረ ነበር (ቁጥር 70)።

የዚህ ድል ውጤቶች ቅድስናና አገልግሎት መሆናቸውን አስተውል (ቁጥር 74–75)። ነፃ ያወጣን ፈቃዳችንን እንድንፈጽም አይደለም፤ ያ ባርነት ይሆናልና፤ ዳሩ ግን ፈቃዱን በመፈጸም በነፃነቱ ደስ እንዲለን ፈትቶናል።

የዕዳ መሰረዝ (ቁጥር 76–77)። «ስርየት» ማለት «ማባረር፥ ዕዳን መሰረዝ» ማለት ነው። ሕጉን ስለተላለፍንና ከመመዘኛዎቹ አንጻር ሕይወታችንን ልንመራ ባለመቻላችን፥ ሁላችንም ለእግዚአብሔር ዕዳ አለብን (ሉቃ. 7፡40–50)። በተጨማሪም፥ ሁላችንም ዕዳችንን ለመክፈል የማንችል መንፈሳዊ ጉስቋሎች ነን። ኢየሱስ ግን ወደ ምድር ወርዶ ዕዳችንን ከፈለልን [ዮሐ. 1፡29፤ መዝ. (103)፡12]።

አዲስ ቀን (78–79)። ሰዎች በጨለማና በሞት መካከል ተቀምጠው የነበሩ ሲሆን፥ ኢየሱስ ሲመጣ በጭንቀት ተወጥረው ነበር፤ ኢየሱስ

ግን ብርሃንን፥ ሕይወትንና ሰላምን አመጣላቸው። ከእግዚአብሔር የፍቅር ምሕረት የተነሣ የአዲስ ቀን ብርሃን አንጸባረቀ (ማቴ. 4፡16)።

ሽማግሌው ካህን ለዘጠኝ ወራት አንድም ቃል አልተነፈሰም ነበር፤ ይሁንና፥ ይህንን የምስጋና መዝሙር ለእግዚአብሔር በመዘመሩ ለዝምታ ዘመኑ ማካካሻ የሚሆን ታላቅ ነገር ተናግሯል። ልጁ ለመሢሑ መንገድ ይጠርግ ዘንድ በመመረጡ ምንኛ ደስ ተሰኝቶ ይሆን? (ኢሳ. 40፡1-3፤ ሚልክ. 3፡1)። ዮሐንስ በማርያም ማኅፀን ውስጥ «በልዑሉ ኃይል» የተጸነሰውን (ቁጥር 35) «የልዑሉን ልጅ» (ቁጥር 32) የሚያስተዋውቅ «የልዑሉ ነቢይ» ነበር (ቁጥር 76)።

ዮሐንስ በካህንነቱ በተመቻቸ ሕይወት ትፍስሕት ሊያደርግ ሲገባው፥ በመንፈሳዊና በሥጋዊ ሁኔታ ራሱን እያሠለጠነ በበረሃ ኖሯል፤ ይህንንም ያደረገው እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለመሢሑ መምጣት እንዲያዘጋጅ መቼ እንደሚልከው ለመጠባበቅ ነበር። እንደ ስምዖንና ሐና የመሳሰሉ ሰዎች ለብዙ ዓመታት ይህንኑ ዕለት ሲጠባበቁ ኖረዋል (ሉቃ. 2፡25-38)፤ ዕለቱም ሊደርስ ተቃርቦ ነበር።

ዛሬ እግዚአብሔር መልካም ዜናውን ተቀብለን እንድናምን ይጠራናል። ይህንኑ ዜና ተቀብለው የሚያምኑ ሰዎች ደስታውን በማግኘት ምስጋናቸውን ሊገልጹለት ይፈልጋሉ። ኢየሱስ አዳኝ ነው ወይም ደግሞ አዳኙ እርሱ ብቻ ነው ማለቱ አይበቃም፤ እንደ ማርያም፥ «ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች» ልንል ይገባል (ሉቃ. 1፡47)።

## - 2 -

# ጌታ መጣ!

## ሉቃስ 2

ምዕራፍ ሁለት ምናልባትም ከሉቃስ ወንጌል ውስጥ በጣም የሚወደድና እጅግ የሚታወቅ ክፍል ሳይሆን አይቀርም። ባለቤቴና እኔ ዱሮ ልጆቻችን ትናንሽ በነበሩበት ጊዜ እንደምናደርገው ሁሉ፥ አሁንም በየዓመቱ በገና ዋዜማ የመጀመሪያዎቹን ሃያ ቁጥሮች አብረን እናነብባለን። ታሪኩ የቆየ ቢሆንም ሁልጊዜም አዲስ ነው፤ የእግዚአብሔርም ሕዝቦች በፍጹም አይሰለቹትም።

ዶክተር ሉቃስ ስለ መጀመሪያዎቹ የኢየሱስ ዓመታት ሦስት ዐበይት ደረጃዎችን ያስነብበናል።

### 1. አዲስ የተወለደው ሕፃን (2፡1–20)።

«እንደ ሕፃን ልጅ ደካማ ነው» የሚለው የምዕራባውያን የተለመደ አባባል በግርግም ተኝቶ ለነበረው ለሕፃኑ ኢየሱስ ሊያገለግል የሚችል አልነበረም። በሰው አባባል እንደ ማንኛውም ሕፃን ደካማ ሲሆን፥ ከሰማያዊ ምንጩ አንጻር ደግሞ የኃይል ሁሉ ማዕከል ነበር።

<u>የእርሱ መወለድ ማርያምና ዮሴፍን ወደ ቤተልሔም ወሰዳቸው</u> (ቁጥር 1–7)። የወቅቱ አገረ ገዥ አውግስጦስ ቄሣር ነበር፤ ይህም ሆኖ እግዚአብሔር ቃሉን ይፈጽም ዘንድ ማርያምንና ዮሴፍን ከናዝሬት አስነሥቶ መቶ ሰማንያ ኪሎ ሜትር ርቃ ወደ ነበረችው ቤተልሔም ለመውሰድ የቄሣርን ትእዛዝ ስለተጠቀመ የበላይ ገዥው እግዚአብሔር ነበር። ሮም ለወታደራዊ ዓላማዎችና ለቀረጥ አከፋፈል ስትል በየአሥራ አራት ዓመቱ ቆጠራ ታካሂድ ነበር፤ በዚህም ጊዜ እያንዳንዱ አይሁዳዊ ወንድ ስሙን፥ ሥራውን፥ ንብረቱንና ቤተሰቡን ለማስመዝገብ ወደ አባቶቹ ከተማ ይመለስ ነበር።

ማርያም «እንደ ቃልህ ይሁንልኝ» (1፡38) ስትል፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሕይወቷ የመለኮታዊ ትንቢት ፍጻሜ አካል ሆኖአል ማለት ነበር። እግዚአብሔር አዳኙ ሰው እንጂ መልአክ (ዘፍጥ. 3፡15፤ ዕብ. 2፡16)፥ አይሁዳዊ እንጂ የአሕዛብ ወገን (ዘፍጥ. 12፡1–3፤ ዘኁል. 24፡17) እንደማይሆን ቀደም ብሎ ተናግሯል። ከይሁዳ ነገድ (ዘፍጥ. 49፡10)፥ ከዳዊት ቤተሰብ (2ኛ ሳሙ. 7፡1–17) በዳዊት ከተማ በቤተልሔም (ሚክ. 5፡2) ከድንግል ይወለድ ነበር (ኢሳ. 7፡14)።

ይህ ሁሉ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈው ትንቢት የተፈጸመ ሲሆን፥ ቄሣርም ሳያውቅ ጠቃሚ ሚና ተጫውቷል። ኤ.ቲ. ፒርሰን፥ «ታሪክ የእርሱ ታሪክ ነው» ሲሉ፥ ፕሬዚዳንት ጀምስ ኤ. ጌርፊልድ ደግሞ ታሪክን «ያልተፈታ የትንቢት ጥቅል ጽሑፍ» ይሉታል። ሕይወታችንን የሚቆጣጠረው የእግዚአብሔር ቃል ከሆነ፥ የታሪክ ክስተቶች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ብቻ ይረዱናል። ጌታ፥ «እፈጽመው ዘንድ በቃሌ እተጋለሁ» ይላል (ኤር. 1፡12)።

ማርያምና ዮሴፍ ወደ ባልና ሚስትነት ደረጃ የደረሱ ቢሆንም፥ እስከ ኢየሱስ ልደት ድረስ የፈቃደ-ሥጋ ግንኙነት ባለማድረጋቸው፥ ማርያም «እጮኛው» ትባል ነበር (ማቴ. 1፡18–25)። መንገዱ እጅግ አድካሚ ሊሆን ቢችልም፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸሟ ተደሰተች፤ እንዲሁም በናዝሬት ከምትሰማው አሽሙር በመራቋም ሳትደሰት አልቀረችም።

በዚያን ጊዜ እናቶች ለልጆቻቸው እግሮችና እጆች ጥንካሬ ጥበቃ ለማድረግ በረዥም የጨርቅ ስብስቦች ይጠቀልሉአቸው ነበር። «ግርግም» ተብሎ የተተረጐመው ቃል በ13፡15ም የተደገመ ሲሆን፥ የከብቶች መመገቢያ ወይም ማደሪያ ስፍራ ሊሆን ይችላል። እስከ ዛሬም ለከብት መመገቢያ ከድንጋይ ጐድጐድ ብለው የተሠሩ ጥንታዊ ግርግሞች በቅድስቲቱ ከተማ ስለሚገኙ፥ ለሕፃኑ ኢየሱስ እንዲህ ዓይነቶቹ ስፍራዎች የመኝታ አልጋ ሳይሆኑለት አልቀሩም። አያሌ ምሁራን ጌታችን የተወለደው ብዙ እንስሳት በሚገኙበት ዋሻ እንጂ በዘመናዊ የግርግም ትእይንቶች ውስጥ በሚታየው ዓይነት የተበረበረ እንጨት ውስጥ እንዳልሆነ ያምናሉ።

«ቤተ ልሔም» ማለት «የእንጀራ ቤት» ማለት ሲሆን፥ ይህም ለሕይወት እንጀራ መወለድ ፍጹም ትክክለኛ ስፍራ ነው (ዮሐ. 6፡35)። ብዙ የታሪክ ውርሷ የራሔልን መሞትና የብንያምን መወለድ (ዘፍጥ. 35፡16–20፤ እንዲሁም ማቴ. 2፡16–18 ተመልከት)፥ የሩትን ጋብቻና የዳዊትን ብዝበዛ ያካትታል። ብንያም ማለት «የቀኝ እጁ ልጅ» ማለት ሲሆን፥ ዳዊት ማለት ደግሞ «የተወደደ» ማለት ነው። እነዚህ ሁለቱም ስሞች ከጌታችን ጋር ይዛመዳሉ፤ እርሱ በእግዚአብሔር ቀኝ [መዝ. (110)፡1] የተወደደ ልጅ ነውና (ሉቃ. 3፡22)።

<u>ልደቱ መላእክትን ከሰማይ ስቧል</u> (ቁጥር 8–14)። መላእክት ፈጣሪው እንደ ፍጡር ሲወለድ፥ ቃል የነበረው እንደማይናገር ሕፃን ሆኖ ሲመጣ ባዩ ጊዜ እንደምን ተደንቀው ይሆን? ለዚህ ከሁሉም የሚልቀው ማብራሪያ 2ኛ ቆሮንቶስ 8፡9 ሲሆን፥ ከልባችን የምንሰጠው

ከሁሉም የሚበልጠው ምላሽ ደግሞ አድናቆትና አምልኮ ነው። «እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤ በሥጋ የተገለጠ...» (1ኛ ጢሞ. 3፡16)።

በመጀመሪያ መልአኩ የመሢሑን መወለድ ያወጀው ላልታወቁ እረኞች ነበር። ለምን ለእረኞች? ለካህናት ወይም ጸሐፍት ለምን አልተናገረም? መልአኩ ወደ እረኞቹ በመሄዱ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለሰው ልጆች ገልጾአል። በእስራኤል እረኞች ከቁጥር አይገቡም ነበር። ሥራቸው ሥርዓታዊ ርኩሰት ማስከተሉ ብቻ ሳይሆን፥ አንዳንድ ጊዜ ለሳምንታት ከመቅደሱ አካባቢ እንዲርቁ ስለሚያስገድዳቸው ሊነጹ አይችሉም ነበር። እግዚአብሔር የሚጠራው ባለጸጎችንና ታላላቆችን ሳይሆን፥ ድሆችንና ዝቅተኞችን ነው (1ኛ ቆሮ. 1፡26–29፤ ሉቃ. 1፡51–53)።

መሢሑ የመጣው መልካም እረኛ (ዮሐ. 10) እና ለዓለሙ ኃጢአት የሚሠዋ የእግዚአብሔር በግ ለመሆን ነበር (ዮሐ. 1፡29)። ምናልባትም እነዚህ እረኞች የሚጠብቁአቸው በጐች ለቤተ መቅደሱ የመሥዋዕትነት አገልግሎት የሚሰጡ ይሆናሉ። ስለ እግዚአብሔር እረኛና በግ የሚነገረው መልካም ዜና በመጀመሪያ ለትሑታን እረኞች መሰጠቱ ተገቢ ነው።

እረኞች በቀላሉ አይታለሉም። ብዙም በሥራ ላይ ሊውል የማይችል አሳብ የማይኖራቸው ተግባራዊ የዓለም ሰዎች ናቸው። መላእክት አይተው ሲሄዱ መሢሑን እንዳገኙት ቢነግሩህ ልታምናቸው ትችላለህ። እግዚአብሔር ተግተው የሚሠሩትን ሰዎች ልጁ ወደ ዓለም እንደመጣ ለመመስከር የመጀመሪያ አድርጐ ተጠቀማቸው።

በመጀመሪያ፥ አንድ መልአክ (ገብርኤል?) ታየና አስደሳቹን አዋጅ ተናገረ፤ ከዚያም የመላእክት የዝማሬ ቡድን አጀበውና የምስጋና አዝማች አፈለቀ። ከብዙ ምእተ ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የእግዚአብሔር ክብር ወደ ምድር ተመለሰ። ደፋሮቹ እረኞች በተመለከቱትና በሰሙት ነገር በፍርሃት ከራዱ፥ በነገሩ እውነተኛነት ልትተማመን ትችላለህ።

«አትፍራ!» የሚለው ከልደት ታሪክ ቁልፍ ጭብጦች አንዱ ነው (1፡13፥30፥74፤ ማቴ. 1፡20 ተመልከት)። የመልአኩ ንግግር በቀጥታ ሲተረጐም፥ «ለእናንተ መልካም ዜና እነግራችኋለሁ፤ ይህም ለሰው ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ ነው» የሚል ይሆናል። መልአኩ «መልካሙን ዜና ለመስበክ» የሚል ሐረግ ተጠቅሟል፤ ይህም ሉቃስ በወንጌሉና በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በብዛት የሚጠቀመው አሳብ

ነው። በዚህ ስፍራ ሉቃስ በዓለም አቀፍ ወንጌል ላይ እንዳተኮረ እንመለከታለን፤ መልካሙ የምስራች ለአይሁዶች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ሰው ነው።

መልካሙ የምሥራች ምን ነበር? እግዚአብሔር የሰውን ከሁሉም የጠለቀ ጉድለት ለመሙላት ወታደር ወይም ዳኛ ወይም የተሐድሶ መሪ ሳይሆን፥ አዳኙን እንደ ላከ ልብ በል። ይህም በብዙ ጦርነት ውስጥ ለነበረ ዓለም የተላከ የሰላም መልእክት ነበር። ከ27 ዓ.ዓ. ጀምሮ ዝነኛው የሮም የሰላም ደንብ («ፓክስ ሮማና») ከሥራ ላይ ቢውልም፥ የጦርነት አለመኖር ለሰላም ዋስትና አልሰጠም።

ስሜቱን አምቆ መከራ በመቀበል የሚታወቀው ፈላስፋ ኤፒክቲተስ፥ «አንድ ንጉሥ በየብስና በባሕር ላይ የሚደረገውን ጦርነት በመግታት ሰላም ሊያመጣ ቢችልም፥ የምኞትን፥ የኃዘንንና የምቀኝነትን ቁርሾ ሊያስወግድ አይችልም። ሰዎች ከጦርነት ከሚረፍ በበለጠ የሚናፍቁትን የልብ ሰላም ሊሰጥ አይችልም» ብሏል።

(ሰላም «ሻሎም») የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጦርነትን ለማቆም ከሚደረግ ስምምነት የላቀ ፍች አለው። ደህና መሆን፥ ጤንነት፥ ብልጽግና ከአደጋ መጠበቅና ሙሉነት ማለት ነው። ከሁኔታዎች ይልቅ ከባሕርይ ጋር ይያያዛል። ያኔ እንደዛሬው ሁሉ ሕይወት አስቸጋሪ ገጽታዎች ነበሩት፤ በወታደራዊው መንግሥት አገዛዝ ሥር ቀረጥ ጣራ ነክቷል። ከፍተኛ ሥራ አጥነትና የሥነ-ምግባር ዝቅጠት ይታይ ነበር። የሮም ሕግ፥ የግሪክ ፍልስፍናና የአይሁድም ሃይማኖት እንኳ የሰውን ልብ መሻቶች ሊያሟሉ አልቻሉም ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆን፥ እግዚአብሔር ልጁን ላከ!

መላእክት በፍጥረት ጊዜ እግዚአብሔርን ያመሰገኑት ሲሆን (ኢዮብ 38፥7)፥ አሁን ደግሞ በአዲሱ ፍጥረት መጀመሪያ ላይ ደግመው ያመሰግኑታል። የደኅንነት ዕቅድ ጠቅላላ ዓላማው ለእግዚአብሔር ክብርን ማምጣት ነው (ኤፌ. 1፥6፥12፥14 ተመልከት)። የእግዚአብሔር ክብር በመገናኛው ድንኳን (ዘፀአ. 40፥34) እና በቤተ መቅደስ ውስጥ አድሮ ነበር (2ኛ ዜና. 7፥1-3)፤ በኋላ ግን ከሕዝቡ ኃጢአት የተነሣ ተለይቶአቸዋል (1ኛ ሳሙ. 4፥21፤ ሕዝ. 8፥4፤9፥3፤10፥4፥18፤11፥22-23)። በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ክብር በልጁ አምሳል ወደ ዓለም እየተመለሰ ነበር (ዮሐ. 1፥14)። ከኢየሱስ መገኘት የተነሣ ያ ግርግም ቅድስተ ቅዱሳን ሆነ!

<u>ልደቱ እረኞችን ከመስከ ሳበ</u> (ቁጥር 15-20)። «እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ» የሚለው ሐረግ እነዚህ ሰዎች ከስፍራው ርቀው እንደ ነበሩ

ይገልጻል፤ ዳሩ ግን አዲስ የተወለደውን መሢሕ ለማየት እዚያ ድረስ ለመጓዝ ፈቃደኞች ነበሩ። ወደ ቤተ ልሔም በጥድፊያ ሲሄዱ ሌሎች ሰዎች መንገዶቻቸውን እንዲጠብቁ ሳያደርጉ አልቀረም። ሐልፎርድ ሉኮክ ይህንኑ ሁኔታ፥ «የመጀመሪያው የገና ጥድፊያ» ብለውታል፤ ዳሩ ግን ይህ ከዛሬው የገና ጥድፊያ የተለየ ነው።

በቁጥር 16 «አገኙ» የሚለው ቃል በፍለጋ ማግኘታቸውን ያመለክታል። እረኞቹ ምን እንደሚፈልጉ ያውቁ ነበር፤ አዲስ የተወለደ ሕፃን በመጠቅለያ ጨርቆች ተጠቅልሎና ከግርግም ተኝቶ ይፈልጉ ነበር። እናም አገኙት! ለሕፃኑ ሰገዱለትና እግዚአብሔርን ለፈጸመው ተአምር፥ ለጸጋውና ለመልካምነቱ አደነቁት።

እነዚህ እረኞች ዛሬ ልንከተላቸው የሚገቡን መልካም ምሳሌዎቻችን ናቸው። እግዚአብሔር የላከላቸውን መልእክት በእምነት ተቀብለው ወዲያው ታዘዙ። ሕፃኑን ካገኙት በኋላ፥ «እግዚአብሔርን እያመሰገኑ» መልካሙን የምስራች ለሌሎች አደረሱ። መላእክቱን ተከተው ዜናውን ሲያበስሩ እንመለከታለን! (ቁጥር 13–14)። ከዚያም በትሕትና ወደ ሥራቸው ተመለሱ፤ ወደ ቀድሞው የተለምዶ ሥራቸው ታድሰው ሄዱ።

በምንም ምክንያት እረኞች በችሎት ፊት እንዲመሰክሩ አይፈቀድላቸውም ነበር፤ እግዚአብሔር ግን የተወሰኑ ትሑታን እረኞች ትንቢቱ እንደተፈጸመና መሢሑ እንደተወለደ የሚናገሩ የመጀመሪያዎቹ ሰብአውያን ምስክሮች አድርጎ ተጠቀመ። መላእክት የእግዚአብሔርን ጸጋ ስላልተለማመዱ ልክ እንደ እኛ ሊመሰክሩ አይችሉም። ለሌሎች ስለ አዳኙ መናገር የጠነከረ ግዴታና ታላቅም ዕድል ስለሆነ፥ አማኞች የሆንን ሁሉ በታማኝነት ልንወጣው ይገባል።

## 2. ሕፃኑ (2፡21–38)።

ሐኪሙ ሉቃስ በኢየሩሳሌም መቅደስ ስለተካሄዱ ሦስት አስፈላጊ ነገሮች ይነግረናል፤ ሕፃኑ ኢየሱስ ከሙሴ (ቁጥር 20–24)፥ ከስምዖን (ቁጥር 25–35) እና ከሐና (ቁጥር 36–38) ጋር ተገናኘ።

<u>ሙሴ</u> (21–24)። ከቁጥር 21–40 «ሕግ» የሚለው ቃል አምስት ጊዜ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰ ልብ በል። ምንም እንኳ ሰዎችን ከሕግ እስራት ነፃ ለማውጣት ቢመጣም፥ ኢየሱስ «ከሕግ በታች» ተደርጎ ነበር፤ የሕግን ትእዛዝ ፈጽሞአል (ገላ. 4፡1–7)። የመጣው ሕግን ሊሽር ሳይሆን ሊፈጽም ነበር (ማቴ. 5፡17–18)።

የኢየሱስ ወላጆች ስምንት ቀናት ሲሆነው እንዲገረዝ በማድረግ ሕጉን ታዝዘዋል። ይህ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን ምልክትና ማኅተም ሲሆን (ዘፍጥ. 17)፥ የሚያምን አይሁዳዊ ሁሉ እርአያነቱን መከተል ነበረበት። አይሁዶች የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ በመሆናቸው ይታበዩና ሌሎችን አሕዛብ «ያልተገረዙ» በማለት ያጥላሉ ነበር (ኤፌ. 2:11-12)። ይህ ጠቃሚ መንፈሳዊ እውነት ያዘለው ሥርዓት ለብዙ አይሁዶች ባዶነት የሞላው ሥርዓት ሆኖ መቀየሩ አሳዛኝ ነገር ነው (ዘዳግ. 10:15-20፤ ሮሜ. 2:28-29)።

የፊላደልፍያ አገልጋይና ደራሲ የነበሩት ዶናልድ ግሬይ ባርንሐውዝ፥ «ግርዘቱ ለእኛ የተቀበለው የመጀመሪያው ሥቃይ ነበር» ብለዋል። ይህም አዳኙ የኃጢአት ተፈጥሮአችንን በማስወገድ በመስቀል ላይ የፈጸመውን ተግባር ያመለክታል (ቈላ. 2:10-11፤ ፊልጵ. 3:1-3፤ ገላ. 6:15)። ለጌታ በመታዘዝ፥ ማርያምና ዮሴፍ «ኢየሱስ» ብለው ሰየሙት፤ ይህም «ያህዌ ደኅንነት ነው» የሚል ፍች አለው (ማቴ. 1:21)።

ይህም ሆኖ፥ ግርዘት የመጀመሪያ ተግባር ብቻ ነበር። ሕፃኑ አርባ ቀናት ሲሞላው ማርያምና ዮሴፍ በዘሌዋውያን ምዕራፍ 12 የተገለጸውን የማንጻት ሥርዓት ለመፈጸም ወደ ቤተ መቅደስ መመለስ ነበረባቸው። እንዲሁም፥ ለማርያም የበኩር ልጅ በመሆኑ «ሊቤዥት» ይገባ ነበር (ዘፀአ. 13:1-12)። አንድ ቀን በውድ ደሙ የሚቤዠንን አዳኝ ለመቤዠት አምስት ሰቅል መክፈል ነበረባቸው (1ኛ ጴጥ. 1:18-19)። ዝቅተኛው መሥዋዕታቸው በግ ለማቅረብ የማይችሉ ድሆች እንደነበሩ ያሳያል (2ኛ ቆሮ. 8:9)። በጉ ግን እርሱ ነበር!

ጌታችን ከሕግ ጋር የነበረው ግንኙነት የማዳን አገልግሎቱ አስፈላጊ አካል ነበር። እርሱ ከሕግ በታች ተደርጓል (ገላ. 4:4)፤ ምንም እንኳ የሰውን ሃይማኖታዊ ወጎች ቢቃወምም፥ የእግዚአብሔርን ሕግ ሙሉ ለሙሉ ፈጽሟል (ዮሐ. 8:46)። ለእኛ የሕጉን ርግማን በመሸከም (ገላ. 3:13) ከእስራት ነፃ አውጥቶናል (ገላ. 5:1)።

<u>ስምዖን</u> (ቁጥር 25-35)። ስምዖንና ሐና እንደ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ሁሉ መሢሓቸውን በጉጉት ከሚጠብቁ አይሁዳዊያን ቅሬታዎች የሚመደቡ ነበሩ (ሚል. 3:16)። ለመሞት ካለው ዝግጁነትና ጉጉት የተነሣ (ቁጥር 29)፥ ብዙውን ጊዜ ስምዖን በጣም እንዳረጀ ሰው ሆኖ ይሣላል። ይህንን የሚደግፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ግን የለም። አፈ-ታሪክ የ113 ዓመታት ዕድሜ እንደነበረው ቢናገርም፥ አፈ-ታሪክ ሊታመኑበት የሚቻል መረጃ አይደለም።

«የእስራኤል መጽናናት» በመሢሓዊ ተስፋ ማለት ነው። ከተለመዱ የአይሁዳውያን ጸሎቶች አንዱ፥ «አቤቱ፥ የእስራኤልን መጽናናት አሳየኝ» የሚል ነበር። ያ ጸሎት ስምዖን ኢየሱስ ክርስቶስን በመቅደስ ውስጥ በተመለከተ ጊዜ ተፈጽሞለታል። ስምዖን በእግዚአብሔር መንፈስ የተመራ፥ በእግዚአብሔር ቃል የተማረና ለእግዚአብሔር ፈቃድ የታዘዘ ሰው ነበር፤ በዚህ ምክንያት የእግዚአብሔርን ማዳን ለማየት ታደለ። ለሰዎች ሞትን ከማየታቸው በፊት የእግዚአብሔር ማዳን የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ማየት ምንኛ አስፈላጊ ነገር ነው።

ከቁጥር 29–32 ስምዖን ኢየሱስን አይቶ የሰጠውን ምላሽ እንመለከታለን። ይህ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ከሚገኙ «የገና መዝሙሮች» አምስተኛውና የመጨረሻው ነው። [ኤልሳቤጥ (1፡42–45)፥ ማርያም (1፡46–56)፥ ዘካርያስ (1፡67–79)፥ መላእክት (2፡13–14)]። በመጀመሪያ ደረጃ፥ ይህ ስምዖን የተስፋ ቃሉን ጠብቆ መሢሑን በመላኩ እግዚአብሔርን የባረከበት የአምልኮ መዝሙር ነው። የጌታን መሢሕ ለማየት በመታደሉ እግዚአብሔርን በደስታ ያመሰግነዋል።

በተጨማሪም፥ መዝሙሩ የደኅንነት ዝማሬ ነው፤ «ዓይኖቼ… ማዳንህን አይተዋልና» (ቁጥር 30)። እንግዲህ ለመሞት ዝግጁ ነበር! «መሰናበት» ተብሎ የተተረጐመው ቃል በግሪክ አያሌ ፍችዎች ሲኖሩት፥ እያንዳንዳቸው ስለ ክርስቲያን ሞት አንዳንድ ነገር ይናገራሉ። ከፍችዎቹም እስረኛን መልቀቅ፥ መርከብን መፍታትና ጉዞ መጀመር፥ የድንኳን መፍረስ (2ኛ ቆሮ. 5፡1–8 ተመልከት)፥ የእንስሳን ከቀንበር መፈታት (ማቴ. 11፡28–30 ተመልከት) የሚሉ ይገኙባቸዋል። ሞት ከዚህ ሕይወት ሸክሞች አላቅቆ ወደ ሚቀጥለው ሕይወት በረከቶች ስለሚመራን፥ የእግዚአብሔር ሰዎች እስከሆንን ድረስ ሞትን አንፈራም።

የስምዖን መዝሙር የወንጌላዊ መዝሙር ሲሆን፥ ይህም በመቅደስ ውስጥ ለሚቆም አይሁዳዊ ያልተለመደ ነገር ነው። ስምዖን ይህ ታላቅ ማዳን ወደ አሕዛብ ሲሄድ ይመለከታል። ሰዎች ሁሉ ይድኑ ዘንድ (2፡10 ተመልከት) ኢየሱስ ከእስራኤል የለቀቀውን የእግዚአብሔርን ክብር ከመለሰ በኋላ ብርሃኑን ለአሕዛብ አዳርሷል። የክርስቶስ ለዓለሙ ሁሉ መራራት ከሉቃስ ዐበይት ጭብጦች አንዱ እንደሆነ ልብ በል።

ከዚያም ስምዖን ምስጋናውን አቁሞ ትንቢት መናገር ጀመረ (ቁጥር 34–35)፤ በትንቢታዊ መልእክቱም ውስጥ ሦስት ጠቃሚ ተምሳሌቶችን ተጠቅሟል፤ ዓለት፥ ምልክትና ሰይፍ።

ዓለት በብሉይ ኪዳን አስፈላጊ የእግዚአብሔር ተምሳሌት ነው [ዘፍጥ. 49:24፤ መዝ. (18):2፤ (71):3]። መሢሑ የተናቀ የማዕዘን ድንጋይ ይሆን ነበር [መዝ. (118):22፤ ሉቃ. 20:17–18፤ የሐዋ. 4:11]፤ የእስራኤልም ሕዝብ ይሰናከሉበታል (ኢሳ. 8:14፡ ሮሜ 9:32)። በኢየሱስ ክርስቶስ ምክንያት፥ ብዙዎች ከእስራኤል ባለማመናቸው ይወድቁና በደኅንነት ይነሡ ነበር። (ስምዖን ስለ ሁለት ሳይሆን አንድ ቡድን ብቻ የሚናገር ይመስላል።) ዛሬም እንኳ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት እስራኤላውያን በመስቀሉ በመሰናከል (1ኛ ቆሮ. 1:23)፥ ኢየሱስ ዓለታቸው እንደሆነ አይረዱም (1ኛ ጴጥ. 2:1–6)።

«ምልክት» የሚለው ቃል «ተአምር» ማለት ነው፤ ይህም የኃይልን መታየት ሳይሆን በይበልጥ የእውነትን መገለጽ የሚያመለክት ይሆናል። በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የሚገኙ የጌታችን ተአምራት ስለ እርሱ ልዩ እውነቶችን ስለሚገልጹ «ምልክቶች» ተብለዋል (ዮሐ. 20:30–31)። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ተአምር ነው፤ ይህም ሆኖ፥ ሰዎች እርሱን በማድነቅ ፈንታ ሲቃወሙትና ሲያጠቁት ይታያል። ልደቱ ተአምር ቢሆንም፥ በዝሙት እንደ ተወለደ አድርገው ያሙት ነበር (ዮሐ. 8:41)። ተአምራቱን በሰይጣን ኃይል እንደሚፈጽም (ማቴ. 12:22–24) እና ባሕርዩም አጠያያቂ እንደሆነ ተናገሩ (ዮሐ. 8:48፥52፤9:16፥24)። በሞቱ ላይ ሲሳለቁ [መዝ. (22):6–8፤ ማቴ. 27:39–44]፥ ስለ ትንሣኤውም ዋሸተዋል (ማቴ. 27:62–66)። ዛሬ እንኳ ሰዎች ምጽአቱን በተመለከተ ሳይቀር ተጻራሪ አሳብ እየሰነዘሩ ናቸው (2ኛ ጴጥ. 3)።

ይሁን እንጂ፥ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገሩበት መንገድ በልባቸው ውስጥ ያለውን ነገር ያሳያል። እርሱ «የደኅንነት ዓለት»ና «የፍርድ ዓለት» ብቻ ሳይሆን (ዳን. 2:34፥45)፥ የሰዎችን ማንነት የሚያሳይ «የመመዘኛ ዓለት»ም ነው። «ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል?» (ማቴ.22:42) ዛሬም ሰው ሁሉ ሊመልሰው የሚገባው አስፈላጊ ጥያቄ ነው (1ኛ ዮሐ. 4:1–3)።

የሰይፍ ተምሳሌት የተሰጠው ለማርያም ብቻ ሲሆን፥ የመሢሑ እናት እንደ መሆኗ የምትቀበለውን ሥቃይና ኃዘን ያመለክታል። (ይህ ማለት ኢየሱስ ከሠላሳ ዓመታት በኋላ አገልግሎቱን ሲጀምር ዮሴፍ ሞቶ ነበር ማለት ነው፤ ይህ ባይሆን ዮሴፍም ይጠቀስ ነበር።) የግሪኩ ቃል ጎልያድ የተጠቀመውን ዓይነት ግዙፍ ሰይፍ ሲያመለክት (1ኛ ሳሙ. 17:51)፥ የግሡ ትርጉም «ባለማቋረጥ እየተወጉ መድማት» ማለት ነው።

በጌታችን ሕይወትና አገልግሎት ማርያም ብዙ የኃዘን ጊዜያት አሳልፋለች፤ ይህም አንድ ዕለት ከመስቀሉ አጠገብ በመቆም ሲሠቃይና ሲሞት እስካየችበት ጊዜ ድረስ የቀጠለ ልምምድ ነበር (ዮሐ. 19፡25–27)። ይህም ሆኖ፥ የእርሷን መሰጠት ሳናሳንስ በምንም ዓይነት የማርያም የግል ሥቃይ የክርስቶስ የማዳን ሥራ አካል ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ለዓለሙ ኃጢአት ሊሞት የሚችለው እርሱ ብቻ ነው (1ኛ ጢሞ. 2፡5–6)።

ለዚህ ተአምራዊ ልጅ እግዚአብሔር የወጠነውን ታላቅ ዕቅድ ዮሴፍና ማርያም ምን ያህል ተረድተው ነበር? የምናውቀው ነገር የለም፤ የምናውቀው ነገር ቢኖር ማርያም እነዚህን ሁሉ ነገሮች ከልቧ አምቃ ታሰላስል እንደነበረ ነው (2፡19፥51)። ይህም ማለት «ነገሮችን በአንድ ላይ ማድረግ» ማለት ነው፤ ማርያም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመረዳት የሚያስችላትን የሆነ ስልት ትፈልግ ነበር። ማርያም የኢየሱስን አሳብ ያልተረዳችበት ጊዜ ነበር (ማር. 3፡31–35)፤ ይህም ሥቃይዋን ይጨምር ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማርያም ለመጨረሻ ጊዜ የተጠቀሰችው በሰገነቱ ላይ ከሌሎች አማኞች ጋር ስትጸልይ ነው (የሐዋ. 1፡14)።

ሐና (ቁጥር 36–38)። የስሟ ፍች «ጸጋ» ማለት ሲሆን፥ በዕድሜ የበለጸገችና ፈሪሃ–እግዚአብሔር ያደረባት መበለት ነበረች። በሉቃስ ወንጌል ስለ ሴቶች የሚናገሩ አርባ ሦስት ማጣቀሻዎች ሲኖሩ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሱት አሥራ ሁለት መበለቶች ሦስቱ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ይገኛሉ (2፡36–40፤7፥11–15፤21፡1–4 እና 18፡1–8ን ተመልከት)። በሉቃስ ዘገባ ውስጥ የሐኪሙን ርኅራኄ በቀላሉ መመልከት ይቻላል።

በዚያን ዘመን ለመበለቶች ኑሮ የዋዛ አልነበረም፤ ከሕጉ ትእዛዝ ባሻገር ብዙውን ጊዜ ገለል ተደርገው ይጣሉና ይበዘበዙ ነበር (ዘፀአ. 22፡21–22፤ ዘዳግ. 10፡17–18፤14፡29፤ ኢሳ. 1፡17)። ሐና በጾምና በጸሎት አማካኝነት «በማምለክ እግዚአብሔርን ለማገልገል» ራሷን ሰጥታ ነበር። ከወገንዋ ከአሴር ነገድ ተለይታ በእግዚአብሔር ተስፋ የተገባለትን መሢሕ እየተጠባበቀች በመቅደስ ውስጥ ትኖር ነበር (1ኛ ጢሞ. 5፡3–16 ተመልከት)።

የእግዚአብሔር ጊዜ ሁልጊዜም እንከን የሌለበት ፍጹም ነው። ሐና ስምዖን እግዚአብሔርን ስለ ሕፃኑ ኢየሱስ ሲያመሰግን ሳለ ደረሰችና አብራው ትዘምር ጀመር። እነዚህ በዕድሜ የገፉ ሰዎች በመቅደስ ውስጥ ሲዘምሩ ማየት ምንኛ ደስ ይል ይሆን? ምስጋናቸው በእግዚአብሔር

መንፈስ ቅዱስ የተነቃቃ በመሆኑ እግዚአብሔር ተቀበለው። ይህም ሆኖ፥ ሐና ከመዘመርም የላቀ ተግባር አከናውናለች፤ የእስራኤልን መቤዠት ለሚጠባበቁ ሌሎች የ«ቅሬታው» ታማኝ አባላትም መልካሙን ዜና አደረሰች። ብዙ ሰዎች መልካሙን የምሥራች በሰሙ ቁጥር ደስታው ይሰራጭ ጀመር።

ሐና ነቢይት ነበረች፤ ይህም ሲባል የእግዚአብሔርን መልእክት የማወጅና የመተርጐም ልዩ ስጦታ ነበራት ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት ሌሎች የሴት ነቢያት የሙሴ እህት ማርያም (ዘፀአ. 15፡20)፥ ዲቦራ (መሳ. 4፡4)፥ ሕልዳና (2ኛ ነገሥት 22፡14)፥ ኖዓድያን (ነህ. 6፡14) እና የኢሳይያስ ሚስት ናቸው (ኢሳ. 8፡3)። ወንጌላዊ ፊልጶስ አራት ሴት ነቢያት ልጆች ነበሩት (የሐዋ. 21፡8-9)።

### 3. ወጣቱ (2፡39-52)።

ሕጉን በሁሉም ነገር ከታዘዙ በኋላ፥ ማርያምና ዮሴፍ ወደ ናዝሬት ተመለሱ፤ ይህች ናዝሬት ጌታ አገልግሎቱን በይፋ እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ ቤቱ ትሆን ነበር። ብዙ አይሁዳውያን ወንዶች ኢየሱስ (ኢያሱ) ተብለው ይጠሩ ነበር፤ ስለሆነም፥ እርሱ «የናዝሬቱ ኢየሱስ» ተብሎ ሲታወቅ (የሐዋ. 2፡22)፥ ተከታዮቹ «ናዝራውያን» ይባሉ ነበር (የሐዋ. 24፡5፤ ማቴ. 2፡23 ተመልከት)። ጠላቶቹ በዚህ ስም ሲሳለቁ፥ ጲላጦስ በመስቀል ላይ ጽፎ ሰቅሎታል (ማቴ. 21፡11)፤ ይሁን እንጂ፥ ኢየሱስ ከሰማይ ሆኖ ሲናገር በዚህም ስም አላፈረም ነበር (የሐዋ. 22፡8)። ሰዎች የተሳለቁበትን (ዮሐ.1፡46) ኢየሱስ ወደ ሰማይ ወሰደውና የከበረ አደረገው!

ኢየሱስ «በስውር ዓመታት» በናዝሬት ምን አደረገ? ኢየሱስ በሥጋ፥ በአእምሮ፥ በማኅበራዊና በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዳደገ ሐኪሙ ሉቃስ ይነግረናል (ቁጥር 40፥52)። በተሠግዎው፥ የእግዚአብሔር ልጅ የመለኮታዊ ባሕርያቱን ሙሉ ግልጋሎት ተወት በማድረግ፥ ራሱን በጠቅላላው ለአብ አስገዝቶአል (ፊልጵ. 2፡11)። በዚህ ስፍራ ማንም ሙሉ ለሙሉ ሊረዳቸውና ሊያብራራቸው የማይችላቸው ጥልቅ ምሥጢራት አሉ፤ ይህም ሆኖ፥ በእምነት ለመቀበል የሚያስቸግሩን አይደሉም።

ከአፈ-ታሪክ ዘገባ በተቃራኒ፥ ኢየሱስ በልጅነቱ ምንም ተአምር አልፈጸመም፤ ምክንያቱም ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ መለወጥ የተአምራቱ መጀመሪያ ነው (ዮሐ. 2፡1-11)። ከዮሴፍ ጋር የአናጺነቱን ሙያ ሲያከናውን የቆየ ሲሆን (ማቴ. 13፡55 እና ማር. 6፡3)፥ ዮሴፍ

ከሞተ በኋላ ሥራውን በበላይነት ሲያካሂድ የነበረ ይመስላል። በማቴዎስ 1፡25 «እስከትወልድ ድረስ» የሚለው ዮሴፍና ማርያም ከዚያ በኋላ ተገቢ የጋብቻ ግንኙነት እንደፈጸሙ ስለሚያመለክት፥ ባለ ትዳሮቹ ሌሎችም ልጆች ወልደው ነበር (ማቴ. 13፡55-56፤ ዮሐ. 7፡1-10)።

ሉቃስ ከጌታችን የልጅነት ሕይወት አንዱን ታሪክ ብቻ ይነግረናል። ማርያምና ዮሴፍ የተሰጡና በየዓመቱ በኢየሩሳሌም የፋሲካ በዓል የሚያከብሩ አይሁዳውያን ነበሩ። የአይሁድ ሰዎች በዓመት ሦስት ጊዜ ለአምልኮ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ ይጠበቅባቸው ነበር (ዘዳግ. 16፡16)፤ ሁሉም ሰው ግን ይህንን የማድረግ ዓቅም አልነበረውም። አንድ ጊዜ ብቻ ለመሄድ ከቻሉ በአብዛኛው የፋሲካውን በዓል ይመርጡት ነበር፤ ይህ በአይሁድ የጊዜ መቁጠሪያ ሠሌዳ ውስጥ በጣም የተከበረ በዓል በመሆኑ ቤተሰቦቻቸውን ከራሳቸው ጋር ለመውሰድ ይሞክራሉ።

ልጆችና ሴቶች ፊትፊት እየቀደሙና የጉዞ ፍጥነት እየተቆጣጠሩ፥ ወንዶችና ወጣቶች ደግሞ ከኋላ እየተከተሉ ሕዝቡ ወደ በዓሉ ይሄዱ ነበር። ብዙውን ጊዜ ዘመዳሞችና ጐረቤታሞች አብረው ይሄዱና በእያንዳንዳቸው ልጆች ላይ ዓይኖቻቸውን ተክለው ይጠብቁአቸዋል። በአሥራ ሁለት ዓመት ዕድሜው ኢየሱስ በቀላሉ ከአንዱ ቡድን ወደ ሌላው ሊሄድና ላይታጣ ይችል ነበር። ዮሴፍ ኢየሱስ ከማርያምና ከሌሎች ልጆች ዘንድ እንዳለ ሲያስብ፥ ማርያም በበኩሏ ከዮሴፍና ከወንዶቹ ወይም ምናልባትም ከአንድ ዘመዳቸው ዘንድ እንዳለ ልታስብ ትችል ነበር።

ስለሆነም፥ የኢየሱስን አለመኖር የተረዱት ከኢየሩሳሌም የአንድ ቀን መንገድ ያህል ከተጓዙ በኋላ ነበር። ወደ ከተማዪቱ ለመመለስ አንድ ቀን ሲወስድባቸው፥ እርሱን ለማግኘት ደግሞ ሌላ ቀን ጠየቃቸው። በእነዚያ ሦስት ቀናት ውስጥ ዮሴፍና ማርያም በጣም ተጨንቀዋል(ቁጥር 48)። ይህ ቃል ጳውሎስ ላልዳኑ እስራኤል የተሰጠውን ሸክም (ሮሜ 9፡2) እና በሲኦል ያልዳኑ ነፍሳት የሚያሳልፉትን ሥቃይ ለመግለጽ አገልግሏል (ሉቃ. 16፡24-25)።

«ዮሴፍና እናቱ» (ቁጥር 43) የሚለው ሐረግ ከድንግል እንደ ተወለደ ሲያስረዳ፥ «አባትህና እኔ» (ቁጥር 48) የሚለው ዮሴፍ የኢየሱስ ሕጋዊ አባት ሆኖ ተቀባይነት ማግኘቱን ያመለክታል (3፡23 ተመልከት)። ከድንግል መወለዱን ለማፍረስ ይህን አሳብ መጠቀም ከተገቢው ደንብ ማለፍ ነው።

ኢየሱስ ሙሉውን ጊዜ በቤተ መቅደስ ውስጥ ያሳልፍ አያሳልፍ የምናውቀው ነገር የለም። ስፍራው ሰላማዊ ሊሆንና ሰማያዊው አባት ሊጠብቀው ይችል ነበር። ዮሴፍና ማርያም ባገኙት ጊዜ ጥያቄዎችን እየጠየቀና መልሶቻቸውን እያዳመጠ በሃይማኖት መምህራን መካከል ተቀምጦ እንደነበረ እናውቃለን፤ መምህራኑም በጥያቄዎቹና በመልሶቹ ተደንቀው ነበር።

የማርያም የፍቅር ተግሣጽ ኢየሱስ አክብሮት የታከለበትን አስገራሚ ምላሽ እንዲሰጥ አደረገ፤ «ስለምን ፈለጋችሁኝ? በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አላወቃችሁምን?» አላቸው (ቁጥር 49)። በሌላ አባባል፥ «በአባቴ ነገሮች ውስጥ» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፤ አሳቡ ግን ያው ነው። ኢየሱስ መለኮታዊ ልጅነቱንና የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም መላኩን እያረጋገጠ ነበር።

«ይገባኛል» እና «ይገባዋል» የሚሉት ቃላት ሁልጊዜም ከጌታችን አፍ አይርቁም ነበር፤ «ልሰብክ ይገባኛል» (ሉቃ. 4:43)፤ «የሰው ልጅ መከራ ሊቀበል ይገባዋል» (ሉቃ. 9:22)፤ «የሰው ልጅ ሊሰቀል ይገባዋል» (ዮሐ. 3:14)። በአሥራ ሁለት ዓመት ዕድሜው ሳይቀር ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም በመለኮታዊ አስገዳጅ ኃይል ተነሣሥቶ ነበር።

ኢየሱስ «በጥበብ ሰላደገ» (ቁጥር 52) በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ዕቅድ ምን ያህል እንደተረዳ በማሰብ እንደነቃለን። በአሥራ ሁለት ዓመት ዕድሜው ሁሉን ያውቅ ነበር ብለን ልናስብ አይገባም። በመሠረቱ ከአባቱ ጋር ኅብረት በመፍጠሩ ከመንፈስ ቅዱስ ሲማር እነዚያን ምሥጢራዊ ጉዳዮች በመረዳት እንዳደገ ጥርጥር የለውም።

አንድ ነገር የተረጋገጠ ነው፤ ይኸውም ዮሴፍና ማርያም የእርሱ ምሥጢር አልገባቸውም። ይህ ስምዖን በነፍሷ እንደሚያልፍ የተናገረው «ሰይፍ» አካል ሲሆን (ቁጥር 35)፥ ልጁ እያደገ ሲሄድ በተደጋጋሚ ሲከሰት ኖሯል። ከዓመታት በኋላ፥ የጌታችን ቤተሰብ በአገልግሎቱ ወቅት አልተረዳውም ነበር (ሉቃ. 8:19-21፤ ዮሐ. 7:1-5)።

ኢየሱስ ወጣቶች ሁሉ ሊከተሉት የሚገባው ግሩም ምሳሌ ነው። በተለያዩ የሕይወት አቅጣጫዎች ሚዛናዊነቱን በጠበቀው መልኩ ሲያድግ (ቁጥር 52) ቅድሚያ የሰጠው የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም ነበር (ማቴ. 6:33 ተመልከት)። እንዴት ማዳመጥና እንዴት ትክክለኛ ጥያቄዎችን ማንሣት እንዳለበት ያውቅ ነበር (ቁጥር 46)። እንዴት መሥራት እንዳለበት የሚያውቅ ሲሆን ለወላጆቹ ይታዘዝ ነበር።

ኢየሱስ በተናቀች ከተማ ብዙ አባላት በነበሩበት ቤተሰብ ውስጥ፥ ምናልባትም ድሆች በነበሩት ወላጆቹ እጅ አደገ። በወቅቱ የአይሁድ ሃይማኖት ያሽቆለቆለ ሲሆን፥ የሮም መንግሥት አገሪቱን በበላይነት ይቆጣጠር ነበር፤ ማኅበረሰቡም በፍርሃትና በለውጥ ማዕበል ውስጥ ይኖር ነበር። ይህም ሆኖ፥ ከአሥራ ስምንት ዓመታት በኋላ ኢየሱስ ከናዝሬት ሲመጣ አብ ስለእርሱ፥ «የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፥ በአንተ ደስ ይለኛል» ብሏል (ሉቃ. 3፡22)።

አብ ስለ እያንዳንዳችንም እንዲሁ እንዲል ልንጸልይ ይገባል!

# – 3 –

# እነሆ የእግዚአብሔር ልጅ!

## ሉቃስ 3–4

ናፖሊዮን በናፓርቴ፥ «ሶቅራጥስ ወደዚህ ክፍል ከገባ ብድግ ብለን በአክብሮት ልንቀበለው ይገባል። ዳሩ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመጣ በጉልበቶቻችን ተንበርክክን ልናመልከው የግድ ነው» ብሏል።

ሐኪሙ ሉቃስ ከዚህ በላይ በቀረበው የታዋቂው የፈረንሣይ ጀኔራል አሳብ መስማማቱ አይጠረጠርም፤ እርሱም ቢሆን በእነዚህ ሁለት ምዕራፎች የናዝሬቱ ኢየሱስ በትክክል የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ይገልጻልና። ሉቃስ የሚያቀርባቸው ምስክሮች ሁሉ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንደሚገልጹ ልብ በል።

### 1. መጥምቁ ዮሐንስ (3፡1–20)።

<u>አመጣጡ</u> (ቁጥር 1–2)። መጥምቁ ዮሐንስ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ ለ400 ዓመታት በእስራኤል ምንም ዓይነት የትንቢት ድምፅ አልተደመጠም። ከእግዚአብሔር ልጅ ጋር የሚዛመድ ማንኛውም ነገር ከዕቅዱ ውስጥ ስለሆነ (ገላ. 4፡4፤ ዮሐ. 2፡4 እና 13፡1)፥ የእርሱ መምጣት የእግዚአብሔር ፍጹም የጊዜ ስሌት አካል ነበር። ጢባርዮስ ቄሣር የነገሠበት አስራ አምስተኛ ዓመት 28 ወይም 29 ዓ. ም. ነበር።

በምዕራፍ 3፡1–2 ሉቃስ የሮምን ንጉሥ አገረ ገዥ፥ ሦስት አራተኛ ክፍል ገዦችን (የአካባቢውን አንድ አራተኛ እጅ የሚገዙ) እና ሁለት አይሁዳውያን ሊቀ ካህናትን ጨምሮ፥ ሰባት የተለያዩ ሰዎችን ጠቅሷል። ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ቃል ከእነዚህ ወደ አንዱም አልተላከም። ይልቁንም፥ የእግዚአብሔር መልእክት ትሑት አይሁዳዊ ነቢይ ወደ ነበረው ወደ መጥምቁ ዮሐንስ መጣ።

<u>እንዴት እንደ መጣ</u> (ቁጥር 3)። በአለባበሱና በሁኔታው ነቢዩ ኤልያስን የሚመስለው መጥምቁ ዮሐንስ (ሉቃ. 1፡17፤ ማቴ. 3፡4፤ 2ኛ ነገሥ. 1፡8)፥ እየሰበከና እያጠመቀ በዮርዳኖስ ወንዝ አካባቢ ወደሚገኘው ስፍራ መጣ። የእግዚአብሔርን መንግሥት ከደጅ መቅረብ በማወጅ (ማቴ. 3፡3)፥ ሕዝቡ ንስሐ እንዲገባ አደፋፍሯል። ከአያሌ ምእተ ዓመታት በፊት እስራኤላውያን የተስፋ ምድራቸውን ለመውረስ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው ነበር (ብሔራዊ ጥምቀት)። አሁን ደግሞ

እግዚአብሔር ከኃጢአታቸው ተመልሰው ወደ መንፈሳዊ መንግሥቱ እንዲገቡ አዘዛቸው።

ዮሐንስ ከኃጢአት ንስሐ ስለ መግባት ከመስበክ የበለጠ ተግባር እንዳከናወነ ልብ በል። በቁጥር 18 «ይሰብክላቸው ነበር» የሚለው ቃል «ወንጌልን መስበክ» ወይም «መልካሙን የምሥራች መስበክ» ማለት ነው። ዮሐንስ ኢየሱስን የእግዚአብሔር በግ (ዮሐ. 1፡29) እንደሆነ በማስተዋወቅ ሰዎች በእርሱ እንዲያምኑ ነግሮአቸዋል። ዮሐንስ ራሱን እንደ ሚዜ፥ ኢየሱስን ግን እንደ ሙሽራ አድርጐ አቅርቧል (ዮሐ. 3፡25–30)። ዮሐንስ ሕዝቡን ከአዳኛቸው ጋር አስተዋውቆ ስፍራ ለመልቀቅ በተሰጠው ዕድል ደስተኛ ነበር።

የዮሐንስ አገልግሎት ከሌሎች ለየት የሚለው በማጥመቁ ነበር (ዮሐ. 1፡25–28፤ ሉቃ. 20፡1–8)። አይሁዶች ከአሕዛብ ወደ ይሁዲነት የሚለወጡትን ሰዎች ያጠምቁ ስለነበር፥ ጥምቀት ለሕዝቡ አዲስ ነገር አልነበረም። ነገር ግን ዮሐንስ አይሁዶችን በማጥመቁ ያልተለመደ ነገር አድርጓል። የሐዋርያት ሥራ 19፡1–5 እንደሚያብራራው፥ የዮሐንስ ጥምቀት ወደፊት ወደ መሢሑ መምጣት ሲመለከት፥ የክርስቲያን ጥምቀት ግን የክርስቶስን የተፈጸመ ተግባር የኋሊት ይመለከታል።

ይህም ሆኖ፥ ከዮሐንስ ጥምቀት የሚልቅ ሌላ ነገር ነበረ፤ ይኸውም መሢሑ የሚያከናውነው ጥምቀት ነው (ቁጥር 16)። አማኞችን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃቸው የነበረ ሲሆን፥ ይህም የተጀመረው በበዓለ ኀምሳ ነበር (የሐዋ. 1፡5፤2፡ከ1 ጀምሮ)። ዛሬ አንድ ኃጢአተኛ በክርስቶስ በሚያምንበት ቅጽበት በመንፈስ ቅዱስ ወደ ክርስቶስ አካል ይጠመቃል (1ኛ ቆሮ. 12፡13)።

«በእሳት መጠመቅ» ምንድን ነው? ይህ በዕለተ በዓለ ኀምሳ የታዩትን «የእሳት ልሳናት» አያመለክትም፤ በሰው ራስ ላይ የሚታዩ የእሳት ልሳናት ጥምቀት ሊባሉ አይችሉም። ዮሐንስ በቁጥር 9 እና 17 ስለ «እሳት» የተጠቀመው ተምሳሌት ፍርድን እንጂ በረከትን አያሳይም። በ70 ዓ.ም. ቲቶና የሮም ወታደሮች ኢየሩሳሌምን በማፈራረስ ሕዝቡን በበታተኑ ጊዜ የእሳት ጥምቀት ደርሶባቸዋል። የማያምኑ ሰዎች ሁሉ ወደፊት በእሳት ባሕር የፍርድን ጥምቀት ይቀበላሉ (ራእ. 20፡11–15)።

<u>ለምን እንደ መጣ</u> (ቁጥር 4–20)። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱት ማብራሪያዎች እግዚአብሔር ለዮሐንስ የሰጠውን አገልግሎት ለመገንዘብ ይረዱናል።

በመጀመሪያ ደረጃ መጥምቁ ዮሐንስ «በምድረ በዳ የሚጮህ ድምፅ» ነበር (ቁጥር 4፤ በተጨማሪም ኢሳይያስ 40፥1-5 እና ዮሐ. 1፥23 ተመልከት)። ዮሐንስ ለንጉሡ መምጫ መንገዶች መዘጋጀታቸውን ለማረጋገጥ ከንጉሡ ቀድሞ እንደሚሄድ አዋጅ ነጋሪ ነበር። በመንፈሳዊ አባባል፥ የእስራኤል ሕዝብ ባለማመን «ምድረ በዳ» ውስጥ ይቅበዘበዝ የነበረ ሲሆን፥ ወደ መንፈሳዊ እውነታ የሚያደርሱ መንገዶችም ተጣመውና ተበላሽተው ነበር። የክህነት አገልግሎት ብልሽት (አንድ ሊቀ ካህን ብቻ ሊኖር ሲገባ ሁለት ሊቀ ካህናት ይሾሙ ነበር)፥ የጸሐፍትና የፈሪሳውያን ሕግ አጥባቂነትና ግብዝነት የሕዝቡን መንፈሳዊ ሕይወት ክፉኛ አዳክሞት ነበር። ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ድምፅ መስማት እጅግ ያስፈልገው ነበር፤ ይህም ታማኝ ድምፅ በዮሐንስ መጣ።

ሕዝቡን ለመሢሑ፥ መሢሑን ደግሞ ለሕዝቡ ማቅረብ የዮሐንስ ተግባር ነበር (ሉቃ. 1፥16-17፥76-77፤ ዮሐ. 1፥6-8፥ 15-34)። ኃጢአትን ሳይናዘዙ በፊት መለወጥ ሊመጣ ስለማይችል፥ ስለ ኃጢአታቸው በመገሠጽ የእግዚአብሔርን ማዳን አወጀላቸው።

በተጨማሪም፥ ዮሐንስ የማይጠቅሙትን ዛፎች ከሚቆርጥ (ቁጥር 9) እና ስንዴውን ከገለባው ለመለየት (ቁጥር 17) ሲል የማጣራት ተግባር ከሚያከናውን ገበሬ ጋር ተወዳድሯል። እንደ ዛሬዎቹ አንዳንድ «ሃይማኖታዊ ኃጢአተኞች» ብዙዎቹ አይሁዶች የአብርሃም ዘሮች በመሆናቸው ብቻ ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚገቡ ያስቡ ነበር (ዮሐ. 8፥31-34፤ ሮሜ 4፥12-17፤ ገላ. 3፥26-29 ተመልከት)። ዮሐንስ ለእነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር ፍሬ በማያሳይ ሃይማኖታዊ ሥርዓት እንደማይደሰትና የነገሮችን «ሥር» አብጠርጥሮ እንደሚመለከት ገልጾአል። በመጨረሻው ፍርድ፥ ከደኅንነት የራቁ ኃጢአተኞች (ገለባ) በእሳት ሲቃጠሉ እውነተኞቹ አማኞች (ስንዴ) በእግዚአብሔር ይሰበሰባሉ።

በቁጥር 7፥ ዮሐንስ ራሳቸውን የሚያጸድቁትን ኃጢአተኞች እሳት ሲመጣባቸው አይተው ከሣር በሚወጡ እባቦች መስሎአቸዋል። ኢየሱስ ደግሞ ፈሪሳዊያንን ከእፉኝቶች ጋር አወዳድሯል (ማቴ. 23፥33)። የራሳቸው ጽድቅና አለማመን የዲያብሎስ ልጆች አድርጓቸዋል (ዮሐ. 8፥44-45፤ ራእ. 20፥2)። ሃይማኖታዊ መሪዎቹ የዮሐንስን መልእክቶች ለመስማትና ጥምቀቱንም ለመቀበል አለመፈለጋቸው እንዴት የሚያሳዝን ነገር ነው (ሉቃ. 20፥1-8)። ራሳቸው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት አለመቻላቸው

ሳያንስ መጥፎ ምሳሌነታቸውና ሐሰተኛ ትምህርታቸው ሌሎችም እንዳይገቡ አግዷል።

መጥምቁ ዮሐንስ አስተማሪም ነበር (ቁጥር 12)። ዮሐንስ በይፋ መስበክ ብቻ ሳይሆን፥ እንዴት አዲሱን እምነታቸውን በተግባር እንደሚያሳዩ በመንገር ለሕዝቡ የግል አገልግሎትም ሰጥቷቸው ነበር (ቁጥር 10-14)። ራስ ወዳዶች እንዳይሆኑ፥ ነገር ግን ያላቸውን ለሌሎች እንዲያካፍሉ ነግሮአቸዋል (የሐዋ. 2:44-45፤ 4:32-37 ተመልከት)።

ቀራጮችም ሳይቀሩ ለምክር ወደ መጥምቁ ዮሐንስ ይመጡ ነበር። እነዚህ ሰዎች ለሮማውያን ስለሚሠሩና ከሕዝቡም ገንዘብ ስለሚበዘብዙ በአይሁዳውያን ተንቀው ነበር። ዮሐንስ ኢየሱስ የቀራጮች ወዳጅ የመሆኑን እውነታ አጉልቶ አሳይቷል (5:ከ27 ጀምሮ፤ 15:1-2፤19:1-10)። ዮሐንስ ሥራቸውን እንዲተው ሳይሆን በታማኝነት እንዲሠሩ ነግሮአቸዋል።

ወታደሮችም እንዲሁ ለሥራቸው አልተኮነኑም ነበር። ይልቁንም፥ ለግል ጥቅም ሲሉ ሥልጣናቸውን ከመጠቀም እንዲታቀቡ ነግሮአቸዋል። ምናልባትም እነዚህ ከመቅደሱ ወይም ከአይሁድ ገዥዎች ከአንደኛው ጋር ግንኙነት የነበራቸው አይሁዳዊ ወታደሮች ይሆናሉ። የሮም ወታደሮች ከአይሁዳዊው ነቢይ ምክር የሚጠይቁ አይመስልም።

ዮሐንስ የሕዝቡን ልብ አዘጋጅቶ ከዚያ በኋላ መሢሑን ለእነርሱ በማቅረብ አገልግሎቱ ታማኝ ነበር። ኢየሱስ «ጌታ» (ቁጥር 4) እና የእግዚአብሔር ልጅ (ዮሐ. 1:34) መሆኑን በግልጽ ተናግሯል። ዮሐንስ ሄሮድስ አንቲጳስን ከሄሮድያዳ ጋር ለመሠረተው የምንዝርና ጋብቻ ስለ ገሠጸው፥ ንጉሡ አሳስሮት በመጨረሻው ራሱን ተቆርጦ ሞተ። ይህም ሆኖ፥ እግዚአብሔር የሰጠውን አገልግሎት በታማኝነት በመፈጸም፥ ሕዝቡ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነው መሢሐቸው ጋር እንዲገናኙ አድርጓል።

## 2. አብና መንፈስ ቅዱስ (3:21-38)።

አንድ ቀን ሰዎች ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ፥ ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ ለመጠመቅ ራሱን አቀረበ፤ ዮሐንስ ግን በመጀመሪያ እምቢ አለው (ማቴ. 3:13-15)። የናዝሬቱ ኢየሱስ የኃጢአት ንስሐ የማያስፈልገው ፍጹም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ያውቅ ነበር። እንግዲህ ለምን ይሆን ኃጢአት የሌለው የእግዚአብሔር ልጅ የተጠመቀው?

በመጀመሪያ ደረጃ፥ በመጠመቁ ሊያድናቸው ከመጣው ኃጢአተኞች ጋር ራሱን አስተባበረ። በተጨማሪም፥ ጥምቀቱ የአገልግሎቱ ይፋዊ ጅማሬ ነበር (የሐዋ. 1፡21-22፤ 10፡37-38)። በዚህ ጊዜ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት አካባቢ ሲሆን (ቁጥር 23)፥ የአይሁድ ሌዋውያን አገልግሎታቸውን የሚጀምሩት በሠላሳ ዓመታቸው ነበር (ዘኁ. 4፡3፥35 ተመልከት)። ይሁንና፥ የጌታችን ቃላት የመጠመቁን ዋነኛ ምክንያት ይገልጹልናል፤ «እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል» (ማቴ. 3፡15)። እንዴት? በዮርዳኖስ ሲጠመቅ በታየው መንገድ! አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የአዲስ ኪዳን ጥምቀት የሞት፥ የቀብርና የትንሣኤ ተምሳሌት በሆነው ውኃ ውስጥ የመጥለቅ ተግባር እንደተከናወነ ያምናሉ። ጌታችን በውኃ መጠመቁ የመቤዠት ሥራም ተምሳሌት ነበር (ሉቃ. 12፡50፤ ማቴ. 20፡22)። እግዚአብሔር «ጽድቅን ሁሉ የፈጸመው» በመስቀል ላይ ባሳለፈው የሥቃይ ጥምቀት ነበር። (በማቴዎስ 3፡15 የተመለከተው ብዙ ቁጥር «ይገባናል» ዮሐንስንና ኢየሱስን የሚያመለክት ሳይሆን፥ አብን፥ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን የሚገልጽ ነው።)

ጌታችን ከውኃው ሲወጣ አብ ከሰማይ ድምፁን በማሰማት እንደ ተወደደ የእግዚአብሔር ልጅ ለይቶታል፤ መንፈስ ቅዱስም በሚታይ የርግብ አምሳል በኢየሱስ ላይ ወርዷል። በሥላሴ የማያምኑ ሰዎች ይህንን ክስተት ለማብራራት ይቸገራሉ።

አብ ከሰማይ ሦስት ጊዜያት እንደተናገረ ከመዘገቡ ክፍሎች ይህ የመጀመሪያው ነው። ሁለተኛው በተራራ ላይ የኢየሱስ መልክ በተለወጠ ጊዜ ሲሆን (ሉቃ. 9፡28-36)፥ ሦስተኛው ከመስቀሉ በፊት በነበረው የመጨረሻ ሳምንት ነበር (ዮሐ. 12፡28)።

ሉቃስ ብቻ ኢየሱስ በዚህ ጊዜ ይጸልይ እንደነበረ ይጠቅሳል፤ ይህም ከጸለየባቸው አያሌ ጊዜያት አንዱ ነው (5፡16፥ 6፡12፤ 9፡18፥ 28-29፤ 11፡1፤ 23፡34፥46)። ፍጹም የሰው ልጅ እንደመሆኑ፥ ኢየሱስ ለፍላጐቶቹ መሟላት በአባቱ ላይ ይደገፍ ነበር፤ የጸለየውም ለዚሁ ምክንያት ነበር።

በዚህ ጊዜ ሉቃስ የኢየሱስን የዘር ሐረግ ለመጥቀስ በመፈለጉ ትረካውን ለጊዜው አቁሞአል። የማቴዎስ የዘር ሐረግ ገለጻ (1፡1-17) ከአብርሃም በመነሣት ወደፊት ወደ ኢየሱስ ሲቀጥል፥ የሉቃስ ግን ከኢየሱስ ጀምሮ ወደ ኋላ ወደ አዳም ይጓዛል። ማቴዎስ የኢየሱስ ሕጋዊ አባት የነበረውን የዮሴፍን የዘር ሐረግ ሲሰጠን፥ ሉቃስ የእናቱን የማርያምን የዘር ሐረግ ይሰጠናል። ቁጥር 23፥ «ኢየሱስ

አገልግሎቱን በጀመረበት ወቅት ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ነበር (ይህም ኢየሱስ የዮሴፍ ልጅ ሲባል)፥ የኤሊ (የማርያም ዘር ማንዘር)... ልጅ ነበር» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። ምንም እንኳ ማቴዎስ አራት ሴቶችን በዘር ሐረግ ዝርዝር ቢጠቅስም (1፡3፥5፥16)፥ ሴቶች በሕጋዊ የዘር ሐረግ ውስጥ ስለማይገቡ ማርያም ራሷ አትጠቀስም ነበር።

በዚህ ስፍራ የዘር ሐረግ በመዘርዘር፥ ሉቃስ ለአንባቢዎቹ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም ተወልዶ የመጣና የሰውን ችግሮችና ጉድለቶች የተጋራ የሰው ልጅ እንደሆነ አስገንዝቦአል። እንዲሁም ማርያምና ዮሴፍ በዳዊት የዘር ሐረግ ውስጥ ስለሚገኙ፥ እነዚህ የዘር ሐረጐች የናዝሬቱ ኢየሱስ ለዳዊት ዙፋን ሕጋዊ መብት እንዳለው ያረጋግጣሉ (ሉቃ. 1፡32-33)።

### 3. ሰይጣን (4፡1-13)።

ጠላትም እንኳ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መቀበል አለበት። «የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ» (ቁጥር 3፥9) የሚለው መላ ምት ሳይሆን ማረጋገጫ ነው። ይህም «የእግዚአብሔር ልጅ እንደመሆንህ መጠን...» ማለት ነው። እንዲያውም፥ የአምላክነቱ እውነታ ለመጀመሪያዎቹ ሦስት ፈተናዎች መሠረት ነበር። ሰይጣን፥ «አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ሆነህ ሳለ ለምን ትራባለህ? ድንጋዮችን ወደ ዳቦነት መለወጥ ትችላለህ» ሲል ሞገተው። ሰይጣን ኢየሱስ መለኮታዊ ኃይሉን ለግል ጥቅሙ በማዋል የአባቱ የአብን ትእዛዝ እንዲተላለፍ ፈለገ።

ኢየሱስ ለምን ተፈተነ? በአንድ በኩል ከአብ ድጋፍ እንደነበረው ሊረጋገጥ ይገባ ነበር (ቁጥር 22)። ኢየሱስ ሁልጊዜም አባቱን ደስ የሚያሰኘውን የሚያደርግ «የተወደደ» ልጅ ነበረ (ዮሐ. 8፡29)። በተጨማሪም፥ ኢየሱስ በፈተናው የጠላትን የማጥቂያ ዘዴዎች በማጋለጥ፥ በምንፈተንበት ጊዜ እንዴት ፈተናችንን ልናሸንፍ እንደምንችል አሳይቶናል። ይህ ገጠመኝ ርኅሩኅ ሊቀ-ካህን የሆነው ጌታችን አሁን ለሚያከናውነው አገልግሎት እንዲዘጋጅ አግዞታል። እኛም ፈታኙን ለማሸነፍ ለሚያስፈልገን ርዳታ ወደ እርሱ ልንመጣ እንችላለን (ዕብ. 2፡16-18፤ 4፡14-16)። የመጀመሪያው አዳም በገነት ስፍራ ተፈትኖ ሲወድቅ የመጨረሻው አዳም በአስቸጋሪ ምድረ በዳ ውስጥ ተፈትኖ በተሳካ ውጤት አልፎአል (ማር. 1፡13)።

እኛም ኢየሱስ ሰይጣንን በተጋፈጠና ባሸነፈ ጊዜ የተጠቀመባቸውን መንፈሳዊ ምንጮች በማንኛውም ጊዜ ልንጠቅም እንችላለን፤

እነዚህም መንፈሳዊ መሣሪያዎች ጸሎት (3፡21)፥ የአብ ፍቅር (3፡22)፥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል (4፡1) እና የእግዚአብሔር ቃል («ተጽፎአል») ናቸው። በተጨማሪም፥ ጠላትን ሙሉ ለሙሉ ያሸነፈና በሰማይ ሆኖ፥ የሚማልድ አዳኝ አለን (ዕብ. 7፡25 ተመልከት)። ምንም እንኳ ሰይጣን የሚፈትነን በሕይወታችን እጅግ የከፋ ነገር ለማምጣት ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ግን እነዚህን አስቸጋሪ አጋጣሚዎች በሕይወታችን ከሁሉም የላቀ ተግባር ለመፈጸም ሊጠቀምባቸው ይችላል። ፈተና ሰይጣን እኛን ለማሸነፍ የሚጠቀምበት መሣሪያ ሲሆን፥ ዳሩ ግን እኛን ለማነፅ የእግዚአብሔር መሣሪያ ሊሆን ይችላል (ያዕ. 1፡1–8፥ 13–17 ተመልከት)።

በመጀመሪያው ፈተና፥ ሰይጣን የአብ ፍቅር ጉድለት እንዳለበት ገለጸ፤ ይህንንም ያደረገው «የተወደደው» ልጁ በመራቡ ምክንያት ነው። ከዚያ በፊት በነበሩት ዓመታት እስራኤላውያን በምድረ በዳ ሲራቡ እግዚአብሔር ከሰማይ እንጀራ አወረደላቸው፤ ስለሆነም ኢየሱስ ራሱን ለመመገብና ነፍሱን ለማቆየት መለኮታዊ ኃይሉን ሊጠቀም ይችል ነበር። ሰይጣን በተዘዋዋሪ መንገድ ይህንኑ አቀራረብ በሔዋን ላይ ተጠቅሟል፤ «እግዚአብሔር አንድ ነገር ሊሰጥሽ አልፈለገም ማለት ነው። ለምን በዔድን ገነት ውስጥ የሚገኘውን አትክልት ሁሉ አትመገቢም? ቢወድሽማ ኖሮ፥ ሁሉንም ነገር ይሰጥሽ ነበር!» አላት።

ይህም ሆኖ፥ ሰይጣን ኢየሱስ ሥጋዊውን ከመንፈሳዊው እንዲለይ እየጠየቀ ስለነበር፥ ፈተናው ይበልጥ ስውር ነበር። በክርስትና ሕይወት መብላትም መንፈሳዊ ተግባር ስለሆነ፥ የዕለት እንጀራችንን ለእግዚአብሔር ክብር ልንጠቀም እንችላለን (1ኛ ቆሮ. 10፡31፤ ሮሜ 14፡20–21)። ሕይወታችንን «ሥጋዊ፥» «ቁሳዊ፥» «ምጣኔ ሀብታዊ፥» ወይም «መንፈሳዊ» እያልን ስንከፋፍል፥ እግዚአብሔርን ከተገቢው የባለቤትነት ስፍራው ገለል እናደርገዋለን። ክርስቶስ በሁሉም ነገር የቀዳሚነቱን ስፍራ መያዝ አለበት፤ አለዚያም በምንም ነገር እንዲሠለጥን አንፈቅድም (ማቴ. 6፡33)። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ በጥጋብ ከመኖር በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ሆኖ መራብ ይመረጣል።

ጌታችን ከዘዳግም 8፡3 ሲጠቅስ አጽንኦት የሰጠው «ሰው» በሚለው ቃል ላይ ነበር። ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ልጅ እንደመሆኑ፥ ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ኃይል ነበረው፤ ዳሩ ግን ትሑት የሰው ልጅ በመሆኑ አብ የፈቀደውን ብቻ የማድረግ ሥልጣን ነበረው። (ዮሐ. 5፡17፥30፤ 8፡28፤ 10፡17–18፤ 15፡10፥15 በጥንቃቄ ተመልከት።) ባሪያ እንደመሆኑ፥ ኢየሱስ ለግል ጥቅሞቹ መለኮታዊ ባሕርያቱን

አልተጠቀመም (ፊልጵ. 2፡5–8)። ሰው ስለነበር ቢራብም፥ አባቱ በራሱ ጊዜና በራሱ መንገድ የሚያስፈልገውን እንደሚሞላለት ያምን ነበር።

እኔና አንተ ለሰውነታችን እንጀራ መብላት ይኖርብናል (ማቴ. 6፡11)፤ ይሁንና በእንጀራ ብቻ መኖር የለብንም። በተጨማሪም መንፈሳዊ ፍላጐታችንን ለማርካት ለውስጣዊ ሰውነታችንም ምግብ እንሻለን። ይህም ምግብ የእግዚአብሔር ቃል ነው [ኤር. 15፡16፤ መዝ. (119)፡103፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡2]። ለሰውነት የምግብ መፈጨት ሂደት እንዳለው ሁሉ ለነፍስም ቃሉን የማሰላሰል ጊዜ አለው። ቃሉን ስናነብና ስናሰላስል ለውስጣዊ ሰውነታችን መንፈሳዊ ጤንነትና ጥንካሬ እናገኛለን፤ ይህም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ያስችለናል።

ሉቃስ ሁለተኛውንና ሦስተኛውን ፈተናዎች ለምን ኋለኛውን ወደፊት እንዳስቀመጠ አናውቅም፤ ይህም ሆኖ፥ ክስተቶችን በቅደም ተከተል እንዳስቀመጠ ስለማይናገር ከማቴዎስ 4፡1–11 ጋር አይቃረንም። በማቴዎስ 4፡5 «ከዚህ በኋላ» የሚለው ቃል የማቴዎስ ቅደም ተከተል ትክክለኛው እንደሆነ ያመለክታል። የሉቃስ የዘገባ ቅደም ተከተል ከ1ኛ ዮሐንስ 2፡16 ጋር የሚመሳሰል ይመስላል፤ ይኸውም የሥጋ ምኞት (ድንጋይ ወደ እንጀራ መለወጥ)፥ የዓይን አምሮት (የዓለም መንግሥታትና ክብራቸው)፥ እንዲሁም በራስ መመካት (ከመቅደስ ጫፍ መዝለል) ነው፤ ሆኖም ሉቃስ ይህንን እያሰበ መጻፉ አጠራጣሪ ነው።

አብ ከዚህ ቀደም ለወልድ የዓለምን መንግሥታት ሁሉ ለመስጠት ቃል ገብቷል (መዝ. 2፡7–8)፤ ከዚያ በፊት ግን ወልድ መከራ መቀበልና መሞት የግድ ያስፈልገው ነበር (ዮሐ. 12፡23–33፤ ራእ. 5፡8–10)። መጀመሪያ መከራ ከዚያ በኋላ ደግሞ ክብር ሊከተል ይገባ ነበር (ሉቃ. 24፡25–27)። ጠላቱ ግን አንድ ጊዜ ብቻ ከሰገደለት እነዚህኑ ነገሥታት እንደሚሰጠውና ወደ መስቀል የመሄዱን አስፈላጊነት እንደሚያስወግድለት ተናገረ (ማቴ. 16፡21–23 ተመልከት)። ሰይጣን ሁልጊዜም የእግዚአብሔርን ስፍራ በመውሰድ አምልኮ ሊቀበል ሲፈልግ ኖሯል (ኢሳ. 14፡13–14)።

የዚህ ዓለም አዛዥ እንደመሆኑ፥ ሰይጣን የተወሰነ ሥልጣን ከእግዚአብሔር ዘንድ ተሰጥቶታል (ዮሐ. 12፡31፤14፡30)። አንድ ቀን ለአጭር ጊዜ ዓለምን ከሚገዛው የዓመፅ ሰው ማለትም ከሐሳዊ መሲሕ ጋር ይህንኑ ሥልጣን ይጋራል (ራእ. 13)። ሰይጣን ለክርስቶስ

መንግሥታትን እንደሚሰጥ መናገሩ የተወሰነ ሥልጣን እንዳለው ቢያመለክትም፥ የተጠቀማቸው ቃላት ግን ተቀባይነት የሌላቸው ነበሩ፤ እናም አዳኙ ለመቀበል አልፈለገም።

አሁንም ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል እንደገና ጠቅሶአል፤ በዚህ ጊዜ የጠቀሰው ከዘዳግም 6፡13 ነበር። ሰይጣን ስለ «አገልግሎት» ምንም ቃል ባይተነፍስም፥ ኢየሱስ ግን የምንሰግድለትን እንደምናገለግል ያውቅ ነበር። ሰይጣንን ማገልገል ከባድ ባርነት ሲሆን፥ እግዚአብሔርን ማገልገል እውነተኛ ነፃነት ነው። የሰይጣን መንገድ በክብር ጀምሮ በመከራ መፈጸም ሲሆን፥ የእግዚአብሔር መንገድ ግን በመከራ ጀምሮ በክብር ማሳረግ ነው (1ኛ ጴጥ. 5፡10)። ሰይጣን ዘላለማዊውን ለጊዜያዊ ነገር ሠውተን ቀላሉን እርምጃ እንድንመርጥ ይፈልጋል።

ይሁንና፥ ለክርስትና ሕይወት ምንም ዓይነት «አቋራጭ መንገድ» የለውም፤ ለመንፈሳዊ ድልና ብስለትም ቀላል መንገድ የሚባል ነገር የለም። ፍጹም የእግዚአብሔር ልጅ በዙፋኑ ላይ ከመቀመጡ በእንጨት ላይ መሰቀል ከነበረበት፥ ደቀ መዛሙርቱ ቀላል የሕይወት መንገድ ያጋጥመኛል ብለው ተስፋ ሊያደርጉ አይገባም (ሉቃ. 9፡22–26 እና የሐዋ. 24፡22 ተመልከት)።

ሰይጣን ኢየሱስ ድንጋይን ወደ እንጀራ እንዲለውጥ በፈተነው ጊዜ የአብን ፍቅር ተጠራጥሮ ነበር። እንዲሁም ለኢየሱስ የዓለምን መንግሥታት ከመስቀሉ ወዲህ በኩል ሲያቀርብ ተስፋውን ተጠራጥሯል (ዕብ. 12፡1–3)። ኢየሱስ ከመቅደስ ላይ እንዲዘልና አብ የተስፋ ቃሉን እንደሚጠብቅ እንዲያረጋግጥ ሲጠይቅ ሰይጣን የአብን ታማኝነት ተጠራጥሮ ነበር [መዝ. (91)፡11–12]። ስለሆነም፥ ጠላት የክርስትና ሕይወት ሦስት መሠረታዊ ምግባራትን ማለትም እምነትን፥ ተስፋንና፥ ፍቅርን አጥቅቷል ማለት ነው።

ምናልባትም የመቅደሱ ጫፍ የሚገኘው ከቄድሮን ሸለቆ ከፍ ብሎ ከመቅደሱ ደቡባዊ ምሥራቅ ጥግ ይሆናል። ሰይጣን በቅድስቲቱ ከተማ ከመቅደሱ ጫፍ በሚገኘው ስፍራ እንኳ ሊፈትነን ይችላል። ሰይጣን የኢየሱስን ተግባር በመኮረጅ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሊጠቅስ ፈለገ፤ ስለሆነም መዝሙረ ዳዊት (91)፡11–12ን መረጠ። ይሁንና፥ የተስፋ ቃሉን ከማዛባቱ ባሻገር «በመንገድህ ሁሉ» የሚለውንም ክፍል አስወግዱል።

የእግዚአብሔር ልጅ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ የአባቱ ጥበቃና እንክብካቤ እንደማይለየው በልበ-ሙሉነት ሊናገር ይችላል። ዳሩ ግን በፈቃዱ ወደ መከራ ራሱን ከጨመረ በኋላ እግዚአብሔር እንደሚያድነው ተስፋ አድርጐ ቢጠባበቅ እግዚአብሔርን እየተፈታተነ ነው (ለዚህ ዘፀአት 17፡1-7ን እንደ ምሳሌ ተመልከት)። እግዚአብሔር ከቃሉ በሚቃረን መልኩ እንዲሠራ ስናስገድደው (ወይም ስንደፍረው) እግዚአብሔርን እንፈታተናለን። ምንም እንኳ እርሱ ታጋሽና ቸር ቢሆንም፥ የእግዚአብሔርን ትዕግሥት መፈታተን አደገኛ ነገር ነው።

የጌታችን ምላሽ፥ «ተብሎ ደግሞ ተጽፎአል» የሚል ነበር (ማቴ. 4፡7)፤ ከዚያም ዘዳግም 6፡16ን ጠቀሰ። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠቅላላ ገለጻ ለማግኘት ቅዱሳት መጻሕፍትን ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ሚዛናዊነቱን በጠበቀ መልኩ አመሳከሯል። ጥቅሶችን ከዓውደ-ንባባቸው፥ ወይም ምንባቦችን ከጠቅላላው የመጽሐፍ ቅዱስ መገለጽ ካወጣህ፥ ማንኛውንም ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ልታረጋግጥ ትችላለህ። ብዙ የሐሰት ትምህርቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ጥቅሶችን ከዚህና ከዚያ እየለቃቀምን ከእግዚአብሔር ትእዛዛትን እንቀበላለን የምንል ከሆነ በእምነት አልተመላለስንም ማለት ነው። ይልቁንም በዕድልና እግዚአብሔርን በመፈታተን እንኖራለን። «በእምነት ያልሆነ ሁሉ ኃጢአት ነው» (ሮሜ 14፡23)፤ እንዲሁም «እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው» (ሮሜ 10፡17)።

ኢየሱስ ከምድር በዳ በድል አድራጊነት ቢመጣም፥ ሰይጣን ተስፋ አልቆረጠም። አዳኙን በመፈተን ከአብ ፈቃድ የሚያስወጣባቸውን ሌሎች አጋጣሚዎች ይፈልግ ነበር። አንድሪው በነር በትክክል፥ «ከጦርነት በፊት እንደምናደርገው ከድልም በኋላ ተግተን ልንገኝ ይገባል» ብለዋል።

## 4. ቅዱሳት መጻሕፍት (4፡14-30)።

በዮሐንስ 1፡19-4፡45 ውስጥ የተመዘገቡት ነገሮች የተፈጸሙት በዚህ ጊዜ ነበር፤ ዳሩ ግን ማቴዎስ፥ ማርቆስና ሉቃስ እነዚህን ነገሮች አልጠቀሱአቸውም። እነዚህም በገሊላ ስለነበረው የጌታችን አገልግሎት የሚናገሩ ሲሆን፥ ሉቃስ ብቻ ወደ አደገበት ወደ ናዝሬት መሄዱን ይጠቅሳል። በዚህ ጊዜ በናዝሬት ስለሚገኘው ተአምር ሠሪ ወሬ ተሰራጭቶ ነበር፤ ስለሆነም ቤተሰቦቹ፥ ጓደኞቹና ጐረቤቶቹ ሊያዩት ጓጉተዋል።

ከብዙ ሕዝብ ጋር ለአምልኮ መገኘት የጌታችን ልማድ ነበር፤ ይህም ዛሬ የእርሱ ደቀ መዛሙርት ሊከተሉት የሚገባ ልማድ ነው (ዕብ. 10፡24–25)። «ሃይማኖታዊ ዘይቤው» እንደተበላሸ ወይም መማር እንደሚያስፈልገው ሊሟገት ሲችል፥ በዕለተ ሰንበት ጉዞውን ወደ ጸሎት ቤት ያቀና ነበር።

የተለመደው የምኵራብ አምልኮ የሚጀመረው የእግዚአብሔርን በረከት በመማጸን ሲሆን፥ ከዚያም ልማዳዊ የዕብራውያን የእምነት መግለጫ በቃል ይነበባል (ዘዳግ. 6፡4–9፤11፡13–21)። ከዚያም ጸሎትና አንባቢው የዕብራይስጥ ቅዱሳት መጻሕፍትን በአረማይክ ቋንቋ እያሳጠረ የሚያቀርብበት የሕግና የነቢያት መጻሕፍት ንባብ ይቀጥላል።

ቀጥሎም ከማኅበረ ምዕመናኑ ወይም ከቦታ ቦታ ከሚዘዋወረው የአይሁድ የሃይማኖት መምህር (ራባይ) አጭር ስብከት ይቀርባል (የሐዋ. 13፡14–16 ተመልከት)። ካህን ካለ አምልኮው በቡራኬ ይፈጸማል። ይህ ካልሆነ ግን ከተራ ምእመናን አንዱ ይጸልይና ጉባኤው ይሰናበታል።

ኢየሱስ መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብ ስብከት እንዲያቀርብ ተጠይቆ ነበር። ያነበበው ምንባብ ኢሳይያስ 61፡1–2ን የሚያጠቃልል ሲሆን፥ ይህም ስለ ራሱ የሚናገር ክፍል ነበር። የአይሁድ የሃይማኖት መምህራን ይህ ስለ መሢሑ እንደሚናገር ያውቁ የነበረ ሲሆን፥ በምኵራቡ ውስጥ የነበሩትም ሰዎች ይህንኑ ይረዱ ነበር። ኢየሱስ በድፍረት ስለ እርሱ በመጻሕፍት እንደተጻፈና «የተወደደችውን የጌታን ዓመት» ሊሰብክ እንደመጣ ሲናገር፥ ምን ያህል እንደተደናገጡ በምናብህ ልትገምት ትችላለህ።

በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው በዘሌዋውያን 25 የተገለጸው «የኢዮቤልዩ ዓመት» ነው። እያንዳንዱ ሰባተኛ ዓመት ምድሪቱ የምታርፍበት «የሰንበት ዓመት» ሲሆን፥ (ከሰባት የሰንበት ዓመታት በኋላ የሚመጣው) እያንዳንዱ ሃምሳኛ ዓመት «የኢዮቤልዩ ዓመት» ይባል ነበር። የዚህ ልዩ ዓመት ዋንኛ ዓላማ የምጣኔ ሀብትን ዘይቤ ማስተካከያ ማድረግ ነበር፤ ይህም ባሪያዎች ነፃ ወጥተው ወደ ቤተሰቦቻቸው የሚመለሱበት፥ የተሸጡ ርስቶች ለመጀመሪያዎቹ ባለቤቶቻቸው የሚዛወሩበትና ዕዳዎች ሁሉ የሚሰረዙበት ነው። በዚህ ጊዜ ሰዎችና እንስሳት በጌታ ደስ ሲሰኙ ምድሪቱ ሳትታረስ ትቆያለች።

ኢየሱስ በምጣኔ ሀብት ወይም በፖለቲካ ረገድ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን በቁሳዊና መንፈሳዊ መልኩ ይህንን ሁሉ ከራሱ አገልግሎት ጋር አዛምዶአል። ከደኅንነት ርቀው ለጠፉ ኃጢአተኞች የደኅንነትን

መልካም የምሥራች፥ ለተጣሉትና የተሰበረ ልብ ላላቸው ፈውስን አምጥቷል። ብዙዎችን ከዕውርነት፥ ከአጋንንት እስራትና ከደዌ ነፃ አውጥቷል። እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ ለእስራኤል ሕዝብ «የኢዮቤልዩ ዓመት» ነበር።

ችግሩ አድማጮቹ ሊያምኑት አለመቻላቸው ነው። የሚመለከቱት የማርያምና የዮሴፍ ልጅ፥ እያዩት በከተማቸው ያደገ ሰው አድርገውት ነበር። በተጨማሪም፥ በቅፍርናሆም ያደረጋቸውን ተአምራት በናዝሬት ከተማ እንዲደግም ፈለጉ፤ እርሱ ግን አላደረገም። «ባለ መድኃኒት ሆይ፥ ራስህን ፈውስ!» የሚለው ሐረግ ትርጉም ይህ ነው። ተአምር አድርግ!

በመጀመሪያ፥ በማስተማሩ ተደንቀው ነበር፤ ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ አድናቆታቸው ወደ ጠላትነት ተቀየረ። ለምን? ምክንያቱም ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቸርነት ለአሕዛብ ሊናገር ስለ ጀመረ ነው። ነቢዩ ኤልያስ አይሁዳዊ መበለቶችን ሁሉ ትቶ በሲዶና የነበረችውን አሕዛብ መበለት ረድቷል (1ኛ ነገሥት 17፡8-16)፤ የእርሱን አገልግሎት የተረከበው ኤልሳዕም አንድ አሕዛብ ለምጻም ፈውሷል (2ኛ ነገሥት 5፡1-15)። የጌታችን የጸጋ መልእክት ከምኩራባቸው ውጭ ሰው ያለ ለማይመስላቸው አይሁዳውያን ተግሣጽ ቢሆንም፥ ንስሐ ሊገቡ አይፈቅዱም ነበር። ይህ የገጠር ልጅ አይሁዶችም ልክ እንደ አሕዛብ በጸጋ መዳን እንዳለባቸው ሲናገር ምን እንደሚሰማቸው አስብ።

የጉባኤው ሕዝብ እጅግ በመቆጣቱ ኢየሱስን ለመግደል እርምጃ ወሰደ። ቅዱስ አገስቲን፥ «እውነትን ለእነርሱ ሲያበራ ወደዱት፤ ዳሩ ግን በሚወቅሳቸው ጊዜ ጠሉት» ብለዋል። ይህ ዛሬ «ለስላሳን ቃል» (ቁጥር 22) እየወደዱ ዳሩ ግን እውነትን ለመጋፈጥ በማይፈልጉ በብዙ ሰዎች ላይ ይሠራል (ዮሐ. 1፡17ን ተመልከት)።

በናዝሬት ከነበሩት ሰዎች አለማመን ባሻገር፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ የተስፋ ቃሉን ለመፈጸም የተላከ መሢሕ፥ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት አውጀዋል። እርሱንና «የተወደደችውን የጌታን ዓመት» የማይፈልጉ ሰዎች አንድ ቀን «ከአምላካችን የበቀል ቀን» ጋር ይፋጠጣሉ (ኢሳ. 61፡2)። ኢየሱስ በዚያች ስፍራ ላይ ማንበቡን ማቆሙ ምንኛ ግሩም ነገር ነው!

## 5. አጋንንት (4፡31-44)።

ኢየሱስ ከናዝሬት ተነሥቶ ዋና መኖሪያውን በቅፍርናሆም አደረገ (ማቴ. 4፡13-16)፤ ይህችም ቅፍርናሆም የጴጥሮስ፥ የእንድርያስ፥ ያዕቆብና የዮሐንስ የመኖሪያ ከተማ ነበረች። በምኵራቡ ውስጥ መደበኛ የማስተማር አገልግሎት ሲሰጥ፥ ሕዝቡም በመልእክቱ ሥልጣን ይደነቁ ነበር (ማቴ. 7፡28-29ን ተመልከት)። በተጨማሪም በአጋንንት ላይ በነበረው ሥልጣን ሕዝቡን አስደንቋል።

በአጋንንት የተያዘው ሰው ወደ ምኵራብ የሚመጣው ለምንድን ነው? ኢየሱስ እዚያ እንደሚገኝ ያውቅ ነበር? ጌታችን አጋንንት ስለ እርሱ እንዲመሰክሩ ስለማይፈልግ ጸጥ እንዲሉ ካዘዛቸው በኋላ ያስወጣቸዋል። በመሠረቱ አጋንንት ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ያውቃሉ (ቁጥር 34፥ 41)፤ ይህን በማወቃቸውም ይንቀጠቀጡ ነበር (ያዕ. 2፡19)።

ከአገልግሎቱ በኋላ ኢየሱስ ወደ ጴጥሮስ ቤት በመሄድ እዚያ ታማ የነበረችውን የጴጥሮስን አማት ፈወሳት። (ሐኪሙ ሉቃስ ‹ከፍተኛ ትኩሳት› እንደነበረባት አስተውሏል።) ዕለተ ሰንበት በጀምበር መጥለቅ ሲገባደድ የፈውስን ተግባር ማከናወን ይቻል ነበር፤ በዚህም ጊዜ አያሌ ሰዎች በሽተኞቻቸውንና ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች ወደ ጴጥሮስ ቤት በማምጣት ኢየሱስ እንዲረዳቸው ጠየቁት። በዚህም ጊዜ ደግሞ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የመሰከሩትን አጋንንት ዝም አሰኛቸው።

ጌታችን በዚህ ጥድፊያ በበዛበት ቀን አካላዊ ዝለት ሳይደርስበት አልቀረም፤ ይህም ሆኖ፥ በቀጣዩ ዕለት ለጸሎት ማልዶ ሊነሣ ችሏል (ማር. 1፡35)። ለአገልግሎት የሚያስፈልገውን ጥንካሬና ኃይል የሚያገኘው በጸሎት ነበር፤ እኛም ይህኑ ልናደረግ ይገባል።

# - 4 -

# ኢየሱስ በሰው ሕይወት ላይ የሚያመጣው ለውጥ

## ሉቃስ 5

ኢየሱስ ለግለሰቦች ሕይወት ግድ ይለው ነበር። ምንም እንኳ እጅግ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰቡበት ስፍራ ቢሰብክም፥ መልእክቱ ሁልጊዜም ወደ ግለሰቦች የሚያነጣጥር ነው፤ እንዲሁም ሰዎችን በግል ለመርዳት ጊዜ ይወስድ ነበር። በዚህ ሁሉ ዓላማው ሰዎችን መለወጥና የይቅርታ መልእክቱን ለሌሎች እንዲያጋሩ መላክ ነበር። በዚህ በአምስተኛው ምዕራፍ ሉቃስ ጌታችን ከአራት ግለሰቦች ጋር መገናኘቱንና እርሱን በማመናቸው ያገኙትን ለውጥ ይገልጻል።

## 1. ጴጥሮስ- ከውድቀት ወደ ስኬት (5፡1-11)።

ይህ በማቴዎስ 4፡18-22 እና ማር. 1፡16-20 ከተዘገበው ክስተት ጋር አንድ ዓይነት አይደለም። በእነዚያ ታሪኮች ጴጥሮስና እንድርያስ ዓሣ በማጥመድ ተግባር ላይ ሲሆኑ፥ እዚህ ግን ሌሊቱን ሁሉ ሲደክሙ አድረው ምንም ዓሣ ባለመያዛቸው መረቦቻቸውን በማጠብ ላይ ነበሩ። (መረቦች ታጥበው ካልተሰጡና ካልደረቁ በስብሰው ይበጣጠሳሉ።) ኢየሱስ ከዚህ በፊት እነዚህን አራት ሰዎች የጠቀሳቸው ሲሆን፥ ከእርሱ ጋር በቅፍርናሆምና በገሊላ አብረው ከተጓዙ በኋላ ወደ ሥራቸው ተመለሱ (ማር. 1፡21-39)። በዚህ ጊዜ ግን ለሙሉ ጊዜ ደቀ መዝሙርነት ጠራቸው።

ከደቀ መዛሙርቱ ቢያንስ ሰባቱ ዓሣ አጥማጆች ሳይሆኑ አይቀሩም (ዮሐ. 21፡1-3)። በአጠቃላይ ዓሣ አጥማጆች ጌታን ለማገልገሉ ስኬታማነት የሚጠቅሙ ብቃቶች እንዳሉአቸው ተመልከት። በባሕር ላይ ለመሥራት ብርታትና ድፍረት፥ ትዕግሥትና ቆራጥነት፥ እንዲሁም ትልቅ እምነት አስፈላጊዎች ናቸው። ዓሣ አጥማጆች አብረው ለመሥራት (መንጠቆዎች ሳይሆን መረቦችን ይጠቀሙ ነበር) እና እርስ በርሳቸው ለመረዳዳት ፈቃደኞች መሆን አለባቸው። ሥራውን በፍጥነትና በተሳካ ሁኔታ ለመፈጸም የሚያስፈልጉትን ዘዴዎች መማር አለባቸው።

ሌሊቱን ሁሉ ዓሣ ለማጥመድ ሞከሬ አንድም ዓሣ መረቤን ባይጉበኘው፥ መረቤን አሽጠው እንደሆነ እንጂ ለሌላ ቀን ዝግጅት

አላጥበውም። እውነተኛ ዓሣ አጥማጅ ግን ተስፋ አይቆርጥም። ኢየሱስ በርካታ ሕዝብ የሚገኝበትን ስፍራ ለማመልከት ታንኳዪቱን እንደ መድረክ በሚጠቀምበት ጊዜ ጴጥሮስ ተግቶ በመሥራት ላይ ነበር። ዶክተር ጄ. ቬርኖን ማክጊ፥ «እያንዳንዱ ምስባክ የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተላለፍና ዓሣ ለመያዝ የሚሞከርበት የማጥመጃ ታንኳ ነው» ብለዋል።

ለዚህ ጥያቄ ሌላም ገጽታ ነበረው፤ ይኸውም ጴጥሮስ ከታንኳዪቱ ውስጥ ተቀምጦ የእግዚአብሔርን ቃል በሚሰማበት ጊዜ «የተማረከ አድማጭ» መሆኑ ነው። «እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው፤ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው» (ሮሜ 10፡17)። በአጭር ጊዜ ውስጥ ጴጥሮስ በእምነቱ መጠቀም ግድ ሆነበት፤ ኢየሱስም ለዚሁ እምነት እያዘጋጀው ነበር። መጀመሪያ፥ ታንኳዪቱን «ጥቂት ፈቀቅ» እንዲያደርጋት ጠየቀው፤ ጴጥሮስ ዝግጁ ከሆነ በኋላ ደግሞ «ወደ ጥልቁ ፈቀቅ በል» ሲል አዘዘው። ጴጥሮስ ጠቃሚ ለማትመስለው የመጀመሪያ ትእዛዝ አዎንታዊ ምላሽ ባይሰጥ፥ ከቶውንም የተአምሩ ተካፋይ አይሆንም ነበር።

ኢየሱስ ታንኳዪቱን በዚያም ላይ ይሠሩ የነበሩትን ሰዎች ሲያዝ ጴጥሮስ ሳይገረም አልቀረም። ኢየሱስ በሙያው አናጺ ሲሆን (ማር. 6፡3)፥ አናጺዎች ስለ ዓሣ ማጥመድ ምን ያውቁ ኖሯል? በገሊላ ባሕር ዓሣ የሚያዘው ጥልቀት በሌለው የማታ ውኃ እንጂ በቀኑ ጥልቅ ውኃ እንዳልሆነ የታወቀ ነበር። ኢየሱስ የሰጠው ትእዛዝ ሁሉ ከጴጥሮስ ሥልጠናና ልምድ የሚቃረን ነበር፤ ቢሆንም ጴጥሮስ ታዘዘው። ቁልፉ በእግዚአብሔር ቃል ማመኑ ነበር፤ «ግን በቃልህ...» (ቁጥር 5)።

በቁጥር 5 «ጌታ ሆይ» ተብሎ የተተረጐመውን ቃል የተጠቀመው ሉቃስ ብቻ ሲሆን፥ የተለያዩ ፍችዎች አሉ፤ እነዚህም ፍችዎች ስለ ሥልጣን የሚናገሩ ናቸው፤ ጠቅላይ አዛዥ፥ የመጠነኛ ችሎት ዳኛ፥ የከተማ ሹም፥ የኮሌጅ ፕሬዚዳንት የሚሉ ፍችዎች አሉት። ምንም እንኳ ጌታ የሚያደርገውን ነገር በሙሉ ባይረዳም፥ ጴጥሮስ ለኢየሱስ ሥልጣን ለመገዛት ፈቃደኛ ነበር። እንዲሁም ብዙ ሕዝብ ከባሕሩ ዳርቻ ሆኖ ይመለከተው እንደነበር አስታውስ።

ሰዎች ለስኬት የሚሰጡት ምላሽ የእውነተኛ ባሕርይ አንዱ መግለጫ ነው። ጴጥሮስና እንድርያስ የተያዘውን ከፍተኛ ዓሣ ለራሳቸው በመውሰድ ፈንታ የሥራ አጋሮቻቸው እንዲካፈሉ ጠሩአቸው። እኛ እግዚአብሔር በቸርነቱ የሰጠንን በረከት ለሌሎች

የምናካፍል አሸንዳዎች እንጂ፥ ለራሳችን ብቻ አፍነን የምናስቀር ደንበኛ ኖች አይደለንም።

## 2. ከበሽተኝነት ወደ ጤንነት (5፡12–16)።

በዚህ ስፍራ ለምጻም የነበረና ሊለወጥ የሚያስፈልገው ሰው ነበር። በአይሁዶች መካከል አያሌ የቆዳ በሽታዎች በለምጽነት ይታወቃሉ። ከዘመናዊ የሕክምና ሥልጣኔ ባሻገር፥ በዓለማችን አሥር ሚሊዮን ሰዎች የለምጽ በሽተኞች እንደሆኑ ይገመታል። አንደኛው የለምጽ ዓይነት የስሜት ሥሮችን (ነርቮችን) ስለሚጎዳ የዚህ በሽታ ተጠቂ ሕመም አይሰማውም። ይህም በቀላሉ በሽታውን በማስተላለፍ የሥጋ ልባሶችን ወደማውደም ይደርሳል። በመሆኑም እጅና እግር ሽባ ሆኖ በመጨረሻም ይቆረጣል።

የሰዎችን በለምጽ መያዝ ለማወቅ ምርመራ ማካሄዱ የአይሁድ ካህን ተግባር ነበር (ዘሌዋ. 13)። በዚህ በሽታ የተለከፉ ሰዎች ለብቻቸው እንዲኖሩ የሚገለሉ ሲሆን፥ «ነጽቷል!» የሚል የካህን አወጅ እስኪሰጣቸው ድረስ ከኅብረተሰቡ ጋር አይቀላቀሉም ነበር። ኢሳይያስ ለምጽን የኃጢአት ተምሳሌት አድርጐ ተጠቅሟል (ኢሳ. 1፡4–6)፤ የዘሌዋውያን ምዕራፍ 13–14 ዝርዝር ትእዛዛት እንደሚያስረዱት የሕዝቡን ጤንነት ከመጠበቁ ይልቅ ሥርዓትን በማስፈጸሙ ላይ የበለጠ ትኩረት ይሰጣል።

እንደ ኃጢአት ሁሉ ለምጽ ከቆዳ የጠለቀ በመሆኑ (ዘሌዋ. 13፡3)፥ በላዩ ላይ በሚደረጉ እንክብካቤዎች ሊፈወስ አይችልም (ኤር. 6፡14 ተመልከት)። እንደ ኃጢአት ሁሉ ለምጽም ወደ ሌሎች የመሰራጨት ባሕርይ አለው (ዘሌዋ. 13፡7–8)፤ ሲሰራጭ ደግሞ ሰዎችን ያረክሳል (13፡44–45)። ከርኩሰቱ የተነሣ ለምጻም ሰው ከማኅበረሰቡ ተገልሎ ለመኖር ይገደድ ነበር (ዘሌዋ. 13፡46)፤ እንዲሁም አንድ ቀን ከደኅንነት ርቀው የጠፉት ኃጢአተኞች ተለይተው በሲኦል ይከማቻሉ። ለምጽ የያዛቸው ሰዎች እንደ «ሙታን» ሲታዩ (ዘኁል. 12፡12)፥ ለምጽ የነካቸው ልብሶች ወደ እሳት ይጣሉ ነበር (ዘሌዋ. 13፡52)። በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ «ከለምጻቸው» ማለትም ከበደላቸው መገላገሉ ለኃጢአተኞች ምንኛ አስፈላጊ ነገር ነው።

ለዚህ ሰው መለወጥ አስፈላጊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ ሰውዬውም ራሱ ለመለወጥ ፈልጎ ነበር። ለምጻሞች ርቀው መኖር ሲገባቸው፥ ይህ ሰው በነፍሱ ስለቆረጠ ሕጉን ተላልፎ ወደ ጌታ ኢየሱስ ዘንድ በግሉ ቀረበ። በወንጌሉ ሁሉ፥ ሉቃስ ኢየሱስ የተጣሉት ሰዎች ወዳጅ እንደሆነና ለርዳታ ወደ እርሱ ሊመጡ እንደሚችሉ በግልጽ ያብራራል። ይህ ሰው በጌታ ፊት ራሱን አዋርዶ ምሕረቱን ጠየቀ።

ይህ ሰው በእግዚአብሔር ኃይልና ጸጋ ተለወጠ! እንዲያውም፥ ኢየሱስ ይህንን ሰው ነከቶታል! ይህም ማለት እርሱ ራሱም ረከሰ ማለት ነበር። ይህ ኢየሱስ ከደኅንነት ርቀው ለጠፉት ኃጢአተኞች ያደረገው ውብ ምሳሌ ነው! እኛ ንጹሐን እንሆን ዘንድ እርሱ ኃጢአት ሆነልን (1ኛ ጢሞ. 2:4፤ 2ኛ ጴጥ. 3:9)። ኢየሱስ ያድነን ዘንድ ምኞት ብቻ ሳይሆን (1ኛ ጢሞ. 2:24፤ 2ኛ ጴጥ. 3:9) የማዳንም ችሎታ አለው (ዕብ. 7:25)። ይህንንም አሁኑኑ ያደርገዋል (2ኛ ቆሮ. 6:2)።

ኢየሱስ ሰውዬው ወደ ካህን እንዲሄድና በዘሌዋውያን ምዕራፍ 14 ለመንጻት የተሰጡትን ደንቦች እንዲፈጽም አበረታታው። የመንጻት ሥርዓቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በተሠዋዎ፥ በሞቱና በትንሣኤው የፈጸመው ሥራ ተምሳሌት ነው። ይህ ሁሉ የሚካሄደው በወራጅ ውኃ ላይ ሲሆን፥ የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ተምሳሌት ነው። ይህ መሥዋዕት ከኃጢአታችን ነፃ ያወጣን ዘንድ ኢየሱስ የግድ መሞት እንዳስፈለገው ያስታውሰናል።

ኢየሱስ ሰውዬው ማን እንደፈወሰው እንዳይናገር ቢያዘውም፥ የነጻው ለምጻም ግን ለጌታ የመመስከር መሻት አደረበት። (ኢየሱስ ለሁሉም ሰው እንድንመሰክር ቢነግረንም፥ እኛ ግን ዝም እንላለን!) ከዚህም ምስክርነት የተነሣ እጅግ ብዙ ሰዎች ለርዳታ ወደ ኢየሱስ መጡ፤ እርሱም የቸርነት አገልግሎት ሰጥቶአቸዋል። ይህም ሆኖ፥ ብዙዎቹ የነፍሳቸውን መዳን ሳይሆን፥ የመፈወስ ኃይሉን ብቻ እንደሚፈልጉ ስለሚያውቅ፥ በእነዚህ በርካታ ሕዝብ ደስተኛ አልነበረም። ብዙውን ጊዜ ሕዝቡን ትቶ ለመጸለይና የአብን ርዳታ ለመፈለግ ጸጥ ወዳለ ስፍራ ይሄድ ነበር። ይህ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሁሉ ሊከተሉት የሚገባ መልካም ምሳሌ ነው።

## 3. ከበደለኛነት ወደ ይቅር ባይነት (5:17-26)።

ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም (ምናልባትም ወደ ጴጥሮስ ቤት) ከተመለሰ በኋላ ሕዝቡ ሲፈውስ ለማየትና ሲያስተምር ለመስማት ወደዚያው

ተሰባሰበ። በተጨማሪም፥ አንድ አዲስ ነገር ሆነ፤ ይኸውም ከኢየሩሳሌም የተሰባሰቡ አንዳንድ የሃይማኖት መሪዎች እርሱ የሚሠራውን ለመመርመር በዚያ ተገኝተው ነበር። ሐሰተኛ ነቢያት ሕዝቡን እንዳያስቱ መከላከል የሽማግሌዎቹ ኃላፊነት ስለሆነ፥ ይህንን የማድረግ ሙሉ ሥልጣን ነበራቸው (ዘዳግ. 13፤18፡15–22)። መጥምቁ ዮሐንስን የጠየቁት ሲሆን (ዮሐ. 1፡19–34)፥ አሁን ደግሞ የናዝሬቱ ኢየሱስን ይመረምሩ ነበር።

ጻፎችና ፈሪሳውያን በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ሲጠቀሱ ይህ የመጀመሪያው በመሆኑ፥ ከእነዚህ ቡድኖች ጋር መተዋወቁ መልካም ነው። «ፈሪሳዊ» የሚለው ቃል «መከፋፈል፥ መለየት» የሚል ትርጉም ካለው የዕብራይስጥ ቃል የተገኘ ነው። ምናልባት ጻፎችና ፈሪሳውያን የበቀሉት የአይሁድ ሕዝብ የሙሴን ሕግ እንዲጠብቁና በዙሪያቸው ከሚገኙ አረማዊ ሕዝቦች እንዲለዩ ካስተማረው ከካህኑ ዕዝራ አገልግሎት ሳይሆን አይቀርም (ዕዝ. 9–10፤ ነህ. 8–9)። የጻፎችና ፈሪሳዊያን ታላቅ ፍላጐት የእግዚአብሔርን ሕግ በመረዳትና በማጉላት ከዕለታዊ ሕይወታቸው ጋር ማዛመድ ነበር።

ይሁንና፥ ብዙም ሳይቆይ እንቅስቃሴው ሕግ–አጥባቂነት ሆኖ በመለወጡ፥ ጌታን በደስታ ለማገልገል እስከማይቻል ድረስ [መዝ. (100)፡2] መሪዎቹ በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ ጭነት ከመሩ። ከዚህም በላይ ብዙዎቹ ፈሪሳውያን ግብዞች ስለነበሩ፥ የሚሰብኩትን ቃል በሕይወታቸው ኖረው አያሳዩም ነበር (ማቴ. 15፡1–20 እና 23፡1–36 ተመልከት)። በተራራው ስብከት (ማቴ. 5–7)፥ ኢየሱስ የፈሪሳውያንን እምነት ከንቱነት አጋልጦአል። እውነተኛ ጽድቅ የልብ ጉዳይ እንጂ የውጫዊ ልምምዶች ብቻ እንዳልሆነ ገልጾአል።

ጻፎችና ፈሪሳውያን ጌታችን ከተገኘባቸው ስብሰባዎች በአንዱ ላይ ለመሳተፍ መረጡ፤ ይህንንም ያደረጉት የእግዚአብሔር ኃይል በተለየ መንገድ ይገለጽ ስለነበረና ኢየሱስ ሽባውን ሰው ይፈውስ ስለነበር ነው። ለምጽ ብልሹነትንና የኃጢአትን ብክለት የሚያመለክት ከሆነ፥ ሽባነት ደግሞ ኃጢአት በሰው ሕይወት ላይ የሚያስከትለው አንካሳነት መግለጫ ነው። ኢየሱስ ግን ሰውዬውን ከመፈወስ የላቀ ተግባር ይፈጽም ነበር፤ የሰውየውን ኃጢአት ይቅር ይልና ለሕዝቡ ስለ ይቅርታ ያስተምር ነበር።

ሽባው ሰውዬ ራሱ ወደ ኢየሱስ ለመምጣት ባይችልም፥ ወደ ኢየሱስ ዘንድ የሚያደርሱትን አራት ሰዎች በማግኘቱ የታደለ ነበር። እነዚህ አራት ሰዎች ወዳጆች እንዴት አንዳቸው ሌላውን ማገልገል

እንደሚኖርባቸውና ምስኪን ኃጢአተኞች ወደ አዳኙ እንዲመጡ ሊረዱ እንደሚገባ በምሳሌነት ያስተምራሉ።

በመጀመሪያ ደረጃ፥ ኢየሱስ እንደሚፈውሰው ያምኑ ነበር (ቁጥር 20)! እግዚአብሔርም የሚያከብረው ይህንኑ እምነት ነው። ለጓደኛቸው ያላቸው ፍቅር በጥረታቸው ስላልተባበራቸው ከበሩ ላይ የተደረደሩትን ሰዎች ጨምሮ ምንም ነገር ተስፋ አላስቆረጣቸውም ነበር። (ተመልካቾች ኢየሱስን ለማግኘት በሚፈልጉ ሰዎች መንገድ ላይ ቆመው መንገዳቸውን ሲዘጉ ምንኛ የሚያሳዝን ነገር ነው! ዘኬዎስም ይኸው ዓይነት ችግር አጋጥሞታል። ሉቃ. 19፡3ን ተመልከት)። በበሩ በኩል መግባት ሳይቻላቸው ሲቀር፥ ከጣሪው ላይ ወጥተው የጣሪውን ጡብ አንስተው ሰውየው ከአልጋው ላይ እንዳለ በጌታ ፊት አወረዱት።

ኢየሱስ ሰውዬውን ወዲያውኑ ፈወሶ ወደ ቤቱ መላክ ሲችል፥ ስለ ኃጢአትና ይቅርታ ለማስተማር አጋጣሚውን ተጠቅሟል። በመሠረቱ፥ «ተነሣና ተመላለስ!» ከማለት «ኃጢአትህ ተሰየረችልህ!» ማለቱ ቀላል ነበር። ለምን? ምክንያቱም ኃጢአቱ በትክክል መሰረይ አለመሰረዩን ሊያረጋግጥ የሚችል የለምና። ኢየሱስ ከባድ አቋም በመውሰድ የሰውዬውን ሰውነት ፈወሰው። ይህም በቤቱ ውስጥ የነበረ ሰው ሁሉ ሊመሰክር የሚችለው ነገር ነው።

የሰውዬው በሽታ የኃጢአቱ ውጤት ነበር? ይህ ሊሆን የሚችል ነገር ቢሆንም፥ በርግጠኛነት የምናውቀው ጉዳይ የለም (ዮሐ. 5፡1–14ን ተመልከት)። የሰውነቱ መፈወስ በውስጡ ለተካሄደው መንፈሳዊ ፈውስ ውጫዊ መረጃ ነበር። ኢየሱስ ሰውነትን ለመፈወስና ኃጢአትን ለማስተሰረይ ሥልጣን እንዳለው በመናገር የሃይማኖት መሪዎችን አስደንቆአቸዋል። ከዚህ በፊት ሕዝቡ የማስተማርና አጋንንት የማውጣት ሥልጣን እንዳለው ያመነ ሲሆን (4፡32፥36)፥ አሁን ግን ኃጢአት ለማስተሰረይ ደግሞ ሥልጣን እንዳለው ተናገረ። ጻፎችና ፈሪሳውያን የፈውሱን ተአምር ለመካድ ባይችሉም፥ ኃጢአት እንደሚያስተሰርይ መናገሩን ግን ከስድብ እንደሚያንስ ንግግር ቆጠሩ! ኃጢአት ሊያስተሰርይ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነበርና። ኢየሱስ የዚህ ዓይነቱን ዓረፍተ ነገር ሲናገር እግዚአብሔር ነኝ እያለ ስለሆነ፥ ሊወገር ይችል ነበር።

በቁጥር 24 በሉቃስ ወንጌል ሃያ ሦስት ጊዜ ተመዝግቦ የሚገኘው የሰው ልጅ የሚል ማዕረግ የመጀመሪያ ጠቀሜታ ተጠቅሶአል። የጌታችን አድማጮች ለዚህ ማዕረግ እንግዳ አልነበሩም። ይህ ማዕረግ ከሰማንያ ጊዜያት በላይ በነቢዩ ሕዝቅኤል ያገለገለ ሲሆን ዳንኤልም

መሢሑን ለማመልከት ተጠቅሞበታል (ዳን. 7፡13፥18)። «የሰው ልጅ» ጌታችን ራሱን ለማመልከት የሚወደው ስም ነበር፤ ይህ ስም በወንጌላት ውስጥ ቢያንስ ሰማንያ ሁለት ጊዜያት ያህል ተጠቅሶአል። አንዳንድ ጊዜ «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለውን የተጠቀመ ቢሆንም (ማቴ. 27፡43፤ ሉቃ. 22፡70፤ ዮሐ. 5፡25፤ 9፡35፤ 10፡36፤ 11፡4)፥ «የሰው ልጅ» የሚለው ግን የበለጠ በግልጋሎት ላይ ውሏል። የአይሁድ ሕዝብ የዚህን ስም መሢሐዊ ባሕርይ ቢያውቁም፥ ሊያድናቸው ከመጣው ሕዝብም ጋር አስተባብሮታል (ሉቃ. 19፡10)። እንደ ብሉይ ኪዳኑ «የሰው ልጅ» ሕዝቅኤል፥ ኢየሱስም እነርሱ በተቀመጡበት ስፍራ ተቀምጧል (ሕዝ. 3፡15)።

ፈውሱ ቅጽበታዊ በመሆኑ ሕዝቡ እግዚአብሔርን አከበረ። ይሁንና፥ ከፈውስም በላይ ሰውዬው ይቅርታንና የተለወጠውን አዲስ ሕይወት ጅማሬ አግኝቷል። የጌታችን ተአምራት ለምስኪኖች ያለውን ርኅራኄና አምላክነቱን ከማሳየታቸውም በተጨማሪ፥ ስለ ደኅንነት ጠቃሚ መንፈሳዊ ትምህርቶችን ገልጸዋል። ተአምራት መንፈሳዊ ዕውርነት ላጠቃቸው ሰዎች በልጁ ብቻ ቢያምኑ እግዚአብሔር ምን ሊያደርግላቸው እንደሚችል ለማስተማር የሚረዱ «መርጃ መሣሪያዎች» ነበሩ።

## 4. ከአሮጌው ወደ አዲሱ (5፡27-39)።

ኢየሱስ ሌዊን ሲጠራው ሦስት ነገሮችን ፈጽሞአል፤ ይኸውም የጠፋውን ነፍስ ማዳኑ፥ ለቡድኑ አዲስ ደቀ መዝሙር መጨመሩና ለሌዊው ጓደኞች፥ ለጸፎችና ለፈሪሳውያን ስለ አገልግሎቱ ለማብራራት አጋጣሚ መፍጠሩ ነበር። ምናልባትም ይህ ክስተት የተፈጸመው ኢየሱስ ሽባውን ሰውዬ ከፈወሰ ብዙም ሳይቆይ ይሆናል፤ ይህንንም ልንል የቻልነው «የባለሥልጣናት ኮሚቴው» ገና በዚያው ስለነበረ ነው (ቁጥር 17)። ኢየሱስም ለሌዊ አዲስ ስም የሰጠው በዚህን ጊዜ ይመስላል፤ ይህም «ማቴዎስ»፥ ማለት «የእግዚአብሔር ስጦታ» የሚል ነበር (6፡15፤ በተጨማሪም ማቴዎስ 9፡9 ተመልከት)።

ማቴዎስ በቀረጥ መሰብሰቢያ መስኮት ላይ ተቀምጦ በዚያ በኩል የሚያልፈውን የንግድ ዕቃ ይቀርጥ ነበር። የቀረጡ መጠን ሁልጊዜም አንድ ዓይነት ስላልነበረ፥ ምግባረ-ብልሹ ሰው በቀላሉ ለራሱ ተጨማሪ ገንዘብ ሊያከማች ይችል ነበር። ቀራጩ በታማኝነት ቢሠራ እንኳ አይሁዶች ለአሕዛብ በመሥራቱ ራሱን እንዳረከሰ በመቁጠር ይንቁት ነበር። መጥምቁ ዮሐንስ ቀረጥን መሰብሰብ በራሱ ኃጢአት እንዳልሆነ የገለጸ ሲሆን (ሉቃ. 3፡12-13)፥ ማቴዎስ ሌባ ስለመሆኑ

ምንም መረጃ የለንም። ለአይሁዶች ግን ሌዊ ኃጢአተኛ ነበር፤ ኢየሱስም ከእርሱና ከኃጢአተኛ ጓደኞቹ ጋር ኅብረት በማድረጉ ተጠረጠረ።

ማቴዎስ ስለ ኢየሱስ ምን ያህል እንደሚያውቅ የተገለጸ ነገር የለም። ይህም ሆኖ፥ ጌታችን ከጴጥሮስና ከሥራ ተባባሪዎቹ ጋር የመሠረተው ጓደኝነት ከቅፍርናሆም ነጋዴዎች ጋር ሳያገናኘው አይቀርም፤ ማቴዎስም ጌታችን በባሕር ዳርቻ ሲሰብክ ሳይሰማው አይቀርም። ማቴዎስ ወዲያውኑ የጌታን ጥሪ በመታዘዝ ሁሉንም ነገር ትቶ ኢየሱስን ተከትሏል። በደኅንነቱ እጅግ ደስ በመሰኘቱ ደግሞ ከእርሱ ጋር አብረው እንዲደሰቱ አያሌ ጓደኞቹን ጋብዞአል (ሉቃ. 15:6፥9፥23 ተመልከት)።

ጻፎችና ፈሪሳውያን መልእክቱን ወይም አገልግሎቱን ባለመረዳታቸው ኢየሱስን ተቹት። ኢየሱስ በባህል ከተከበበው ከባሕላዊ የሃይማኖት ሕይወታቸው ጋር አይስማማም ነበር። መሪዎች እግዚአብሔር የሚፈጽማቸውን አዳዲስ ነገሮች ለመረዳት አለመሞከራቸው እና ለውጥን መቃወማቸው አሳዛኝ ነገር ነው። እነዚህ ሰዎች ኢየሱስ የሚያደርገውን ይረዱ ዘንድ አራት ምሳሌዎችን ሰጣቸው።

ሐኪሙ (ቁጥር 31–32)። ጻፎችና ፈሪሳውያን ማቴዎስና ጓደኞቹን እንደተኮነኑ ኃጢአተኞች ሲመለከቱ፥ ኢየሱስ ግን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንደታመሙና የሐኪም እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው «በሽተኞች» አድርጎ ተመለከታቸው። እንዲያውም፥ ለምጻሙን ሲያነጻና ሽባውን ሲፈውስ ይህንኑ እውነት አብራርቷል። ኃጢአት ልክ እንደ በሽታ ነው፤ በአናሳና ስውር መንገድ ይጀምራል፤ በድብቅ ያድጋል፤ ጥንካሬአችንን ይወስዳል፤ ሕክምና ካልተደረገም ይገድላል። ሥጋዊ ሰውነትን መግደሉ አሳዛኝ ነገር ሲሆን፥ ኃጢአት ነፍስን ለሲኦል መኮነኑ የበለጠ አሳዛኝ ነው።

ጻፎችና ፈሪሳውያን የሌሎችን ጉድለቶች ለመመርመር ሲጣደፉ፥ የራሳቸውን ግን ለማየት ታውረዋል፤ ምክንያቱም እንደ ሌላው ሰው ሁሉ እነርሱም ኃጢአተኞች ነበሩና። ከውጭ ጻድቃን መስለው ሲታዩ (ማቴ. 23:25–28) ከውስጥ ግን ኃጢአተኞች ነበሩ። እንደ ጠፋው ልጅ ዓይነት የሥጋ ኃጢአት ላይኖርባቸው ቢችልም፥ ዳሩ ግን እንደ ታላቅ ወንድሙ መንፈሳዊ ኃጢአት የተጸናወታቸው ናቸው (ሉቃ. 15:11–32፤ 2ኛ ቆሮ. 7:1)።

ይህን ምዕራፍ በምጽፍበት ጊዜ፥ አንዲት ሴት ከካናዳ ስልክ ደውላ ከሬድዮ መልእክቴ ጋር እንደማትስማማና «አክራሪ የፍርድ ሰዎችን» አጥብቃ እንደምትቃወም በተደጋጋሚ ገለጸችልኝ። ከቃሉ እየጠቀስሁ ላስረዳት ሞከርሁ፤ ብሞክርም ግን ልትቀበል አልፈለገችም። እንደ እርስዋ አባባል ሲኦል የሚባል ነገር የለም፤ እኔም ስለዚያ የመስበክ መብት የለኝም። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ስሰጣት መቀበል አቅቷት ዘጋችብኝ፤ ማድረግ የምችለው ነገር ቢኖር ሐዘን በተሞላው ልብ ለእርሷ መጸለይ ነበር።

የኃጢአትን በሽታ ለማዳን የመጀመሪያው እርምጃ ጉደለት እንዳለብንና ለዚሁም መፍትሔ አንድ ነገር ማድረግ እንደሚገባን ማመን ነው። ሐሰተኛ ነቢያት እውነት ወደማይሆን ተስፋ የሚመራ የውሸት ምርመራ ያካሄዳሉ (ኤር. 6፡14)፤ የእግዚአብሔር ባሪያ ግን ስለ ኃጢአት፥ ሞትና ሲኦል እውነቱን በመናገር ብቸኛውን መፍትሔ ያቀርባል፤ ይህም ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው። የጻፎችና ፈሪሳውያን ሃይማኖት ለማቴዎስ ወዳጆች ምንም ዓይነት ተስፋ ሊሰጣቸው አይችልም ነበር፤ ኢየሱስ ግን ይህንን ሊያደርግ ችሏል።

ኢየሱስ ምንኛ ድንቅ ሐኪም ነው! በፍቅር ወደ እኛ ይቀርባል፤ ይጠራናል፤ ስናምነው ያድነናል፤ እንዲሁም ዕዳችንን ይከፍልልናል። ሁልጊዜም ምርመራው ትክክል፥ መድኃኒቱም ፍጹምና የተሟላ ነው። ስለሆነም ማቴዎስ እጅግ ተደስቶ መልካሙን የምሥራች ለወዳጆቹ ለመናገር መፈለጉ አያስደንቅም።

<u>ሙሽራው</u> (ቁጥር 33–35)። ጻፎችና ፈሪሳውያን ያዘኑት በደቀ መዛሙርቱ ወዳጆች ብቻ ሳይሆን፥ ከኢየሱስና ከሕዝቡ ጋር ኅብረት በማድረግ እጅግ በመደሰታቸው ጭምር ነበር። ከዚህ ሁኔታ ፈሪሳውያን በሃይማኖት ልምምዳቸው አነስተኛ ደስታ ብቻ እንደሚያገኙ እንረዳለን (ማቴ. 6፡16 እና ሉቃ. 15፡25–32 ተመልከት)። ኢየሱስ የተናቀ ሰው ቢሆንም (ኢሳ. 53፡3)፥ በደስታ የተሞላ ሕይወት ነበረው (ሉቃ. 10፡21፤ ዮሐ. 15፡11 እና 17፡13)።

የአይሁድ ሰርጐች ለሳምንት ያህል የሚቆዩ ሲሆን፥ ታላቅ ደስታ እና ፌሽታ የሚስተዋልባቸው ጊዜያት ነበሩ። ኢየሱስ ይህንን ተምሳሌት በመጠቀም ለተቺዎቹ፥ «እኔ የመጣሁት ሕይወትን ወደ ሰርግ በዓል ለለውጥ እንጂ የለቅሶ ቤት ላደርግ አይደለም፤ ሙሽራውን ካወቃችሁ ደስታውን ልትካፈሉ ትችላላችሁ» እያለ ነበር አንድ ቀን እንደሚወሰድ የተናገረ ሲሆን፥ ይህም ተቀባይነት ማጣትንና መሞትን

ያመለክታል፤ በመሀሉ ግን ኃጢአተኞች ወደ ንስሐ መምጣታቸው ስለነበር ለደስታ የሚያበቃ ምክንያት ነበር።

ጾም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ብዙ ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፥ በአዲስ ኪዳን ግን በየትኛውም ስፍራ አልታዘዘም። ይህም ሆኖ፥ የነቢያትና የቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ለዛሬዎቹ አማኞች ጠቃሚ ነው። በማቴዎስ 6፡16–18 የተጠቀሱት የጌታችን ቃላት እንደምንጾም («ስትጦም» ይላል እንጂ «የምትጦም ከሆነ» አይልም) የሚያመለክቱ ሲሆኑ፥ የሐዋርያት ሥራ 13፡1–3 እና 14፡23 የመሳሰሉ ምንባቦች ጾም የቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን ልምድ አካል እንደነበረ ያሳያሉ (በተጨማሪም 1ኛ ቆሮ. 7፡5፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡5፤11፡27 ተመልከት)።

<u>ልብስ</u> (ቁጥር 36)። ኢየሱስ የመጣው አሮጌውን ለመጠገን ሳይሆን አዲሱን ለመስጠት ነበር። ፈሪሳውያን የአይሁድ ሃይማኖት የሚገባውን ያህል እንዳላደገ በማሰብ፥ ኢየሱስ ጥንታዊውን ሃይማኖት በማነቃቃቱ በኩል አብሮአቸው እንደሚሠራ ተስፋ ሳያደርጉ አልቀሩም። ዳሩ ግን ኢየሱስ ሁለቱን ልብሶች ማለትም አዲሱንና አሮጌውን በማነጻጸር የዚህን አመለካከት ሞኝነት አሳይቷል። ከአዲሱ ጨርቅ መጣፊያ ወስደህ በአሮጌ ላይ ብታደርግ ሁለቱም ልብሶች ይበላሻሉ። አዲስ ልብስ ለአሮጌው መጣፊያነት በመዋሉ ሲበላሽ፥ አሮጌው ደግሞ ከእርሱ የማይስማማ መጣፊያ ስለተጨመረበት በሚታጠብበት ጊዜ ተቀዶ ይለያል።

በመጽሐፍ ቅዱስ አልባሳት አንዳንድ ጊዜ ባሕርይንና ጠባይን ለማመልከት አገልግለዋል (ቈላ. 3፡8–17)። ኢሳይያስ ስለ «ጽድቅ መጐናጸፊያ» በመግለጽ (ኢሳ. 61፡10፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡21 ተመልከት) ለደኅንነት በመልካም ሥራችን ላይ መደገፍ እንደሌለብን አስጠንቅቆአል (ኢሳ. 64፡6)። ብዙ ሰዎች ክርስቶስ በጸጋው የሚሰጣቸውን የደኅንነት መጐናጸፊያ በእምነት ከመቀበል ይልቅ የራሳቸውን «የመጣፊያ» ሃይማኖት ያዘጋጃሉ።

<u>የወይን አቁማዳዎች</u> (ቁጥር 37–39)። ያልፈላ ወይን ባረጀ የወይን አቁማዳ ውስጥ ቢጨምር እየፋ አቁማዳውን ያፈነዳና ወይኑም አቁማዳውም ከጥቅም ውጪ ይሆናሉ። አዲሱ የመንፈስ ሕይወት ወደ አሮጌው የአይሁድ የወይን አቁማዳ ውስጥ በግድ ሊገባ አይችልም። ኢየሱስ ጥንታዊ የአይሁድ ሃይማኖት እንዳረጀና በቅርቡም በሌላ እንደሚተካ እየተናገረ ነበር (ዕብ. 8፡13 ተመልከት)። አብዛኞቹ አይሁዶች አሮጌውን በመምረጥ አዲሱን አንቀበልም ብለው ነበር። የአይሁድ ሃይማኖት በሕጉ እንደተገለጸው ወደ ፍጻሜ የደረሰው 70

ዓ.ም ሮማውያን ኢየሩሳሌምንና መቅደሱን ባፈረሱ ጊዜ ነበር። ዛሬ አይሁዶች ክህነት፥ መቅደስ ወይም መሠዊያ ስለሌላቸው፥ እንደ ቅድመ አባቶቻቸው ሃይማኖታቸውን ማካሄድ አይችሉም (ሆሴ. 3፡4 ተመልከት)።

በሕግ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለተፈጸሙ፥ ዛሬ መሥዋዕቶች፥ ካህናት፥ መቅደሶችና ሥርዓቶች አስፈላጊዎች አይደሉም። የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ለጌታ መንፈሳዊ መሥዋዕት የሚያቀርቡ ካህናት ናቸው (1ኛ ጴጥ. 2፡5፥9)። የሕግ ጽላቶች በሰው ልብ ጽላቶች ተለውጠዋል፤ በዚህም ስፍራ የእግዚአብሔር መንፈስ ቃሉን በመጻፍ ኢየሱስ ክርስቶስን እንድንመስል ያደርጋል (2ኛ ቆሮ. 3፡1–3፥18)።

ኢየሱስ ክርስቶስ አሁንም ሁሉንም ነገር አዲስ ያደርጋል (ራእ. 21፡5)። ሐኪም እንደመሆኑ፥ ለኃጢአተኞች አዲስ ሕይወትና መንፈሳዊ ጤንነት ይሰጣቸዋል። እንደ ሙሽራም አዲስ ፍቅርንና ደስታን ያመጣል። የጽድቅን መጐናጸፊያና የመንፈስን የወይን ጠጅ ይሰጠናል (ኤፌ. 5፡18፤ የሐዋ. 2፡13 ተመልከት)። ሕይወት ደስታ የጐላባት በዓል እንጂ፥ መቃብር ቤት ወይም የረሃብ ሰቆቃ አይደለችም፤ በሕይወታችን ውስጥ የዚህ ዓይነቱን ለውጥ ሊያመጣ የሚችለውም ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።